22_1992.pdf

25_1993.pdf

26_1993.pdf

27_1993.pdf

28_1994.pdf

29_1994.pdf

30_1994.pdf

32_1996.pdf

33_1996.pdf

34_1994.pdf

35_1996.pdf

36_1996.pdf

37_1996.pdf

38_1996.pdf

39_1996.pdf

40_1996.pdf

| | |
|---|---|
| ፭ኛ ዓመት ቁጥር ፪<br>5th Year No. 2 | ሐረር ግንቦት ፱ ቀን 1992<br>Harar May 17/2000 |

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

## HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONEL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 0-50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጥር 272 |



ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 22/1992

የሐረሪ ህዝብ ክልል የጤናና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 22/1992.......................................ገፅ 185


**አዋጅ ቁጥር 22/1992 የሐረሪ ህዝብ ክልል የጨናና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ::**

የሐረሪ ህዝብ ክልል የጨናና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀፅ 26 ንኡስ አንቀፅ 2 (ሀ) መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል::

1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የሐረሪ ህዝብ ክልል የጨናና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 22/ 1992 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2.ማሻሻያ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የጨናና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል::

1- በአዋጁ በተለያዩ በታዎች ላይ የሰፈረዉ «የሐረሪ ህዝብ ክልል» የሚለዉ አረፍተ ነገር «የሐረር ከተማ» በሚል ተቀይሯል::

2- በአዋጁ በተለያዩ በታዎች ላይ የሰፈረዉ « ሸንጎ ቤት» የሚለዉ ቃል « መጸዳጃ ቤት » በሚለዉ ተተክቷል::

3- ክፍል አንድ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 ተሰርዟል::

4- ክፍል አንድ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 26 ቀጥሎ የሚከተሉት ንዑስ አንቀፅ 27 እና 28 ተጨምሯል::

« 27. « የስልጣን ክልል » ማለት:- ባለስልጣኑ በሐረር ከተማና ከከተማዉ ክልል ዉጭ ሌሎች አግባብ ካላቸዉ አካላት የቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት የሚንቀሳቀስበት ክልል ማለት ነዉ:: »

«28. « የአገልግሎት ክልል » ማለት:- የሐረር ከተማ ማለት ነዉ::»

5- ክፍል 1 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ተሰርዟል::

6- ክፍል1 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዟል::

7- ክፍል 2 አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 6,7,8,9 ተሰርዟል::

8- ክፍል 3 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 1-ለ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል::

« አንድ ሰራ አስኪያጅ ይኖረዋል::»

www.chilot.me

9- ክፍል 3 አንቀፅ 18 ስር ያሉ ንኡስ አንቀፆች ተሰርዘዉ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች ተተክቷል።

1- የቦርዱ ተጠሪነት ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

2- የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን የክልሉ መንግስት በሚያወጣዉ ደንብ ይወሰናል።

3- የቦርዱ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ።

ሀ- የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር ................................ሰብሳቢ

ለ- የኢኮኖሚ ዘርፍ ኃላፊ ....... አባል

ሐ- የዉ/ል/ማ/ኢ/ቢሮ ኃላፊ ... አባል

መ- የሥ/ክ/ል/ቢሮ ኃላፊ ....... አባል

ሠ- የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም .............................. አባል

ረ- እንደ አስፈላጊነቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰይመዉ አንድ አባል .............................. አባል

ሰ- የባለስልጣኑ ስራ አስኪያጅ ... ፀሀፊ እና አባል

10- ክፍል 3 አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚከተለዉ መልኩ ተሻሽሏል።

«የባለስልጣኑን የስራ እቅድ መርምሮ ይወስናል፡ እንደ አስፈላጊነቱ ከክልሉ መንግስት ድጎማ በጀት ሲጠይቅ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል። »

11- ክፍል 3 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1.2.3.4 ተሰርዘዋል።

12- ክፍል 5 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዘዋል።

13- ክፍል 5 አንቀፅ 33 በሚከተለዉ መልኩ ተሻሽሏል።

«አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 6 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

ሐረር ግንቦት 8 ቀን 1992 ዓ.ም

ጋዚሊ መሐመድ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

6ኛ ዓመት ቁጥር 4
6[th] Year No. 4

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993
HARAR JULY 25/2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 2.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 25/1993
የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 25/1993. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ገጽ 229

## አዋጅ ቁጥር 25/1993 ዓ.ም
## የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ብሔራዊ ክልላችንን ብሎም ሀገራችንን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት አላቆ ኢኮኖሚያችንን ያለማቋረጥ እንዲያድግና የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ትርጉም ባለው አኳኋን ለማሻሻል በሚደረጉት የልማት ጥረቶች የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚኖረው ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑና ለተቃና የኢንቨስትመንት ፖሊሲ አተገባበር እንቅስቃሴው የሚመራበት ወጥና ግልፅ የሆነ አሠራር በማስፈለጉ፣

በክልላችን የተጀመረውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ይበልጥ ለማጠናከር በኢንቨስትመንት ፖሊሲው የአፈጻጸም ሂደት እንዲሁም እንቅስቃሴው ላይ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች አስወግዶ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተለያየ ሙያዊ ዕውቀት የሚጠይቅና መድበለ ዘርፋዊ ባህሪይ ያለው የልማት ተግባር እንደመሆኑ መጠን ለእንቅስቃሴው ስኬታማነትና ስምረት የተቀነባበረ የማበረታቻ አገልግሎት በዝቅተኛ አስተዳደራዊ ወጪና በተቀናጀ ተቋማዊ ድጋፎች ማቅረብና የተቀላጠፈ የአመራር ሥርዓቶች ለመዘርጋት በአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 መሠረት የተቋቋመውን የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት አንጻራዊ ነጻነት ባለው አስተዳደር እንዲተዳደር ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ጽ/ቤት ሆኖ እንደገና ማቋቋም አላማውን ሥልጣኑንና ተግባሩን እንደገና መወሰን በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ቁጥር 52 ንዑስ

www.chilot.me

አንቀፅ 2 እና በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሰረት ከዚህ የሚከተለዉ ታዉጇል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1/ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ « የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤትን እንደገና ለማቋቋምና የሚተዳደርበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 25/1993» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2 ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ዉስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር

1. « ኢንቨስትመንት» ማለት አዲስ ድርጅት ወይም ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይንም ለማሻሻል በባለሃብት የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነዉ።
2. «ድርጅት» ማለት ለትርፍ ሲባል የተቋቋመ ድርጅት ነዉ
3. «ካፒታል» ማለት የሚተላለፍ ሰነድ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሣሪያ ፣ ህንጻ ፣ ማደሻ ፣ የሥራ ማስኬጃ የባለቤትነት መብት የፓቴንት መብት ወይም ሌላ የንግድ ሀብት ነዉ።
4. «ሰዉ» ማለት ማንኛዉም የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ።
5. «የኢንቨስትመንት አዋጅ» ማለት የፌደራል መንግስት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 37/1988 እና የዚህ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 116/1990 ናቸዉ።
6. «ክልል» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ።
7. «ጽሕፈት ቤት» ማለት የክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ነዉ።
8. «ቦርድ» ማለት የኢንቨስትመንትን እንቅስቃሴ በበላይነት እንዲመራ እንዲያስተባብርና እንዲቆጣጠር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8/1/ ላይ የተመለከተዉ አካል ነዉ።
9. «ኮሚቴ» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነዉ።
10. «የክልሉ ም/ቤት» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
11. «የሚመለከተዉ አካል» ማለት በዚህ አዋጅ ዉስጥ ስለተጠቃለሉት ጉዳዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኃላፊነቱ የሚመለከተዉ የማዕከላዊ መንግስት ወይም የክልል መንግስት ወይም በህግ ሥልጣን የተሰጠዉ ሌላ አካል ነዉ።
12. «ደንብ» ማለት የህን አዋጅ ለማስፈፀም በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚወጣ ደንብ ነዉ።
13. «ፍቃድ» ማለት የኢንቨስትመንት ፍቃድ ነዉ።
14. «ባለሃብት» ማለት በክልሉ ኢንቨስት ያደረገ ባለሃብት ወይም እንደቃሉ አገባብ ለሃገር ዉስጥና ለዉጭ ባለሃብት በኢንቨስትመንት አዋጅ አንቀፅ 2/5/ እና በማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 2/6/ የተሰጠዉን ትርጉም ይይዛል።

## 3 ስለ መቋቋም

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ከዚህ በኃላ «ጽ/ቤት»


www.chilot.me

እየተባለ የሚጠራ እራሱን የቻለና ህጋዊ ሰዉነት ያለዉ ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

## 4 ዓላማ

በኢንቨስትመንት አዋጅ አንቀፅ /4/ ከተመለከተዉ በተጨማሪ ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

ሀ/ የክልሉን ህብረተሰብ በምግብ ራሱን እንዲችል ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማጠናከር።

ለ/ የክልሉን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት ኢንቨስተሮችን ማበረታታት።

ሐ/ የክልሉን የገቢ ምንጭ ማሳደግ።

መ/ ወደ ዉጭ የሚላኩ የክልሉ ምርቶች በመጠን፣ በጥራትና በዓይነት እንዲያድግ ማበረታታት።

ሠ/ ለክልሉ ህብረተሰብ የሥራ ዕድል መክፈት።

ረ/ የክልሉን ማህበራዊ አገልግሎት ማጎልበትና የኢኮኖሚ እድገቱን ማበረታታት።

ሰ/ የክልሉን ህብረተሰብ በተለይም ግብርናና ኢንዱስትሪ እንዲሁም የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማበረታታት።

# ክፍል 2

# ሥልጣንና ተግባር

## 5 ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾችና አግባብነት ባላቸዉ ሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆነዉ ጽ/ቤቱ የሚከተለዉ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የክልሉን የኢንቨስትመንት ጉዳዮች ይመረምራል እንቅስቃሴዎችን ያበረታታል ፣ ያስተባብራል ፣ ያስፋፋል፣
2. ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሊወሰዱ የሚገቡ የፖሊሲና የአፈፃጸም እርምጃዎችን ያመነጫል ለቦርድ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
3. የክልሉን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አዲስ መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ ያገናኛል ፣ ይተነትናል ፣ ያሰራጫል ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በግብርና ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በኮንስትራክሽን፣ በመንገድና ትራንስፖርት ወ.ዘ.ተ መስኮች ያስተዋዉቃል፣
4. የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ይህንን አዋጅ ተንተርሶ ለሚዘጋጀዉ ደንብ የአፈፃጸም መመሪያ በማዉጣት በቦርዱ ያጸድቃል፣
5. ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በባለሃብትና በመንግስታዊ መ/ቤቶች በመስተዳድሩና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸዉ መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣
6. ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዱ ዕሁፎችን ፣ መግለጫዎችን ፣ ፊልሞችን እና የመሳሰሉትን ያዘጋጃል ያሰራጫል፣
7. ከባለሃብት የሚቀርቡትን የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን መርምሮ በማጥናት ለክልሉ ልማት ይጠቅማል ተብሎ ለታመነበት ፍቃድ በተጠየቀ በ10 ቀናት ዉስጥ ይሰጣል የማበረታቻ ጥያቄዎችም ላይ ይወስናል፣
8. ፍቃድ የተሰጣቸዉ ባለሃብቶች ፍቃዱ የያዛቸዉ ግዴታዎችና ሁኔታዎች መከበራቸዉን ያረጋግጣል ፍቃዳቸዉንም ይመዘግባል ይይዛል፣

9. የጽ/ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ ይይዛል፣

10. ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ያጋጠሙ ከአቅም በላይ የሆኑትን ችግሮችና ይለያል ከነመፍትሄ ሃሳቡ ለቦርዱ ያቀርባል ፣

11. በህጉ መሰረት ለክልሉና ለህብረተሰቡ ጠቃሚ ያልሆኑትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄዎችን ይካላከላል ይቆጣጠራል፣

12. ሌሎች ከበላይ አካል የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናዉናል::

## ክፍል 3

## አደረጃጀትና ሥራ አመራር

### 6 አደረጃጀትና ተጠሪነቱ

1. ጽ/ቤቱ የሚከተለዉ አደረጃጀት ይኖረዋል:-

ሀ/ ቦርድ ፣

ለ/ የጽ/ቤት ኃላፊና ፣

ሐ/ ለሥራዉ የሚያስፈልጉ ሰራተኞች ይኖሩታል::

2. ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለፕሬዘዳንቱ ይሆናል::

### 7 አሿሿም

የጽ/ቤቱ ኃላፊ በክልሉ ኮሚቴ አቅራቢነት በምክር ቤት ይሾማል::

### 8 የቦርዱ አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. ቦርዱ በኮሚቴዉ ይቋቋማል ጽ/ቤቱም በዚሁ ቦርድ ይመራል::

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለኮሚቴዉና ለክልሉ ፕሬዘዳንት ይሆናል::

3. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመንና አበል ኮሚቴዉ በሚያወጣዉ ደንብ ይወሰናል::

### 9 ስለ ቦርድ አባላት

የቦርዱ አባላት ስብጥር እንደሚከተለዉ ይሆናል:-

ሀ/ የክ/ፕሬዘዳንት ______________ ሰብሳቢ

ለ/ የክ/ኢኮኖሚ ዘርፍ ____________ ም/ሰብሳቢ

ሐ/ የክ/ማህበራዊ ዘርፍ ____________ አባል

መ/ የክ/ኢንቨስት/ጽ/ቤት ኃላፊ__ፀሐፊና አባል

ሠ/ የክ/ፐ/ኢ/ /ል/ቢሮ ኃላፊ______ አባል

ረ/ የክ/ሥ/ከ/ል/ቢሮ ኃላፊ________ አባል

ሰ/ የክ/ግብርና ቢሮ ኃላፊ__________ አባል

ሸ/የክ/ኢ/ት/ን/ቱ/ቢሮ ኃላፊ________ አባል

ቀ/ የክ/ዉ/ማ/ኢ/ቢሮ ኃላፊ_________ አባል

### 10 የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል:-

1. በብሔራዊ ደረጃ የሚወጡ የኢንቨስትመንት አዋጆችና ደንቦችን ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ስለመተግበራቸዉ ያረጋግጣል:: አፈፃጸማቸዉንና የጽ/ቤቱን ተግባራት በበላይነት ይቆጣጠራል ይከታተላል::

2. ከኢንቨስትመንት አዋጅ አፈፃጸም ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይ ዉሳኔ ይሰጣል ወይም ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል::

3. በዚህ አዋጅና በኢንቨስትመንት አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በበላይነት ይቆጣጠራል::

4. ኮሚቴዉ በሚያወጣዉ ደንብ መሰረት ከሚፈቀደዉ የተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ በመወሰን ለሚመለከተዉ አካል አቅርቦ ያፀድቃል:: ለተሰጡት


www.chilot.me

ማበረታቻዎች መመሪያ ያወጣል ተግባራዊነታቸዉንም ይቆጣጠራል።

5. በደንቡ መሰረት የሚደረጉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችንና ድጋፎች ያስተባብራል በሚመለከተዉ አካል መፈጸማቸዉን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

6. የቦርዱ አባላትን ያቀፈ አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ተጠሪነታቸዉም ለሰብሳቢዉ ይሆናል።

7. በክልሉ ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የሚሆን መሬት ኢንቨስትመንቱ ስለሚካሄድበት አካባቢና በሚኖረዉ ጠቀሜታ እንዲሁም እየገመገመ በጨረታ ፣ ያለጨረታ ፣ በድርድርና በነፃ የሚሰጠዉን መሬት ይወስናል አፈፃጸሙንም በበላይነት ይከታተላል።

8. እንደየሁኔታዉ የሚወጡትን አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም እራሱ ቦርዱ የሚያወጣቸዉን መመሪያዎች ኢንቨስተሮች በግልፅ እንዲያዉቁት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል አፈፃጸሙንም ይከታተላል።

9. ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ለማበረታታትና ለማስተባበር እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በየጊዜዉ እየመረመረ አግባብ ባለዉ አካል ያስወስናል።

10. ከፍቃድ ፣ ከማበረታቻና ከመሬት አሰጣጥ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ባለሃብቶች የሚያቀርቡትን አቤቱታና ይግባኝ ተቀብሎ ይወስናል።

11. የጽ/ቤቱን መዋቅር መርምሮ ለኮሚቴ ያቀርባል ፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል።

12. የጽ/ቤቱን ዓመታዊ የስራ እቅድና በጀት መርምሮ ለኮሚቴ ያቀርባል ፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል።

13. ጽ/ቤቱ ለሚሰጠዉ አገልግሎት የሚያስከፍለዉን ክፍያ ይወስናል።

14. ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸዉን መመሪያዎች ሴሚናሮች ወርክሾፖች ጥናቶችና የአሰራር ስልቶች በየጊዜዉ እየመረመረ ዉሳኔ ይሰጣል።

15. የዚህን አዋጅና የኢንቨስትመንት አዋጅ አፈፃጸም በበላይነት ይቆጣጠራል ይከታተላል።

16. በክልሉ የሥልጣን ክልል ዉስጥ ለሚሰጡ ማበረታቻዎች መመሪያ ያወጣል ተግባራዊነታቸዉንም ይቆጣጠራል።

17. ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተገኙ ዉጤቶችን ይገመግማል ተገቢዉንም እርምጃ ይወስዳል።

18. በዚህና በሌሎች አዋጆችና ደንቦች መሠረት በቦርዱ የተላለፉ ዉሳኔዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በኮሚቴዉ ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል።

## 11 ስለ ቦርዱ ስብሰባዎች

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸዉም ጊዜ በቦርዱ ሰብሳቢ አማካኝነት አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምላዓተ ጉባኤ ይሆናል።

3. የቦርዱ ዉሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምጹ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወዳለበት ወሳኝ ይሆናል።

4. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ስርዓትና ደንብ ያወጣል።

www.chilot.me

## 12 የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣን፣ተግባርና ኃላፊነት

1. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዘዳንትና ለቦርዱ ሆኖ የጽ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና አስተዳደር ለማከናወን ኃላፊና የበላይ ተጠሪ ይሆናሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤት ኃላፊ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡
   - ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 5 እና በሌሎች አንቀጾች እንዲሁም አግባብነት ባላቸዉ ሌሎች ህጎች መሰረት ለጽ/ቤቱ የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር ያከናዉናል፡፡
   - ለ/ የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቄሴ ያቅዳል ፣ ያደራጃል ፣ ይመራል ፣ ይቆጣጣራል፡፡
   - ሐ/ ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ጽ/ቤቱን ይወክላል፡፡
   - መ/ ለጽ/ቤቱ የተፈቀደዉን በጀት በፋይናንስ ደንብ እና መምሪያ መሠረት ያስተዳድራል ተፈላጊ የሆኑትን ሠራተኞች በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ መሠረት እንዲቀጠሩ ያደርጋል፡፡
   - ሠ/ የጽ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 13 የገቢ ምንጭ

ጽ/ቤቱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-

1. ከክልሉ መንግስት ከሚመደብ በጀት፣
2. ከሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ ፣
3. ከማናቸዉም ሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገቢ ፣ አርዳታና ስጦታ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣዉ ደንብ ይወሰናል፡፡

# ክፍል አራት

# ስለ ኢንቨስትመንት ፍቃድና ተያያዥ ጉዳዮች

## 14 የፍቃድ ማመልከቻ

የፍቃድ ማመልከቻ ለዘሁ ተግባር በተዘጋጀዉ ቅጽ ላይ ተሞልቶ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተያይዞ ለጽ/ቤቱ መቅረብ አለበት፡-

1. ስለ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መግለጫ ፣
2. ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገባ የሚፈልጉትን መሳሪያዎችና እቃዎች ዓይነትና ብዛት የሚያሳይ ዝርዝር፣
3. የንግድ ማህበር ሲሆን የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ፣
4. ማቋቋም ማስፋፋት ወይም ማሻሻል ሲሆን የዚሁ አጭር መግለጫና የአፈፃጸም ፕሮግራም ፣
5. የዉጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ሲኖሩ ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ስለሚሰጠዉ የሥልጠና ፕሮግራምና ስለሚተኩበት የጊዜ ገደብ፣
6. ማመልከቻዉ በወኪል የቀረበ ሲሆን የዉክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ፣
7. እንደ ፕሮጀክቶቹ ልዩ ፀባይ አግባብ ያላቸዉ ሌሎች መረጃዎች፡፡

## 15 ስለ ፍቃድ አሰጣጥ

1. በሥራ ላይ ያሉትን የፌደራልና የክልሉን ህጎች የማይቃረን መሆኑን በተለይም

www.chilot.me

የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት በወጡ ህጎች የተደነገጉ ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑን በአሥር ቀናት ዉስጥ አረጋግጦ ጽ/ቤቱ ለአመልካቹ ፍቃድ ይሰጣል::

2. ፍቃድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-
ሀ/የባለሐብቱን ሥምና ዜግነት፣
ለ/የኢንቨስትመንቱን የሥራ መስክ፣
ሐ/ኢንቨስትመንቱ የሚካሄድበትን አካባቢ፣
መ/የኢንቨስትመንቱን የካፒታል መጠን ፣
ሠ/አግባብ ያለዉ የኢንቨስትመንት አካል ያስፈልጋል ብሎ ያመነባቸዉ ሌሎች ዝርዝሮች ፣

3. ፍቃዱ የተሰጠዉ ባለሃብት የኢንቨስትመንቱ ፕሮጀክት ግንባታ አጠናቆ ማምራት ወይም አገልግሎት መስጠት እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ የንግድ ወይም የሥራ ፍቃድ እንዲያወጣ አይጠበቅበትም ፣

4. ጽ/ቤቱ ሳይፈቅድ ፍቃድ ለሌላ ሰዉ ማስተላለፍ አይችልም ፣

5. ፍቃዱ ለሌላ ሰዉ ሲተላለፍ ወይም በያዙት ላይ ሌሎች ለዉጦች ሲያጋጥሙ ጽ/ቤት በመቅረብ ማሻሻል አለበት::

## 16 የፍቃድ እድሳት

1. ፍቃዱ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እስከ ሚጀምርበት ድረስ በየዓመቱ መታደስ አለበት ሆኖም ስለኢንቨስትመንቱ አፈፃጸም ሂደት በየስድስት ወሩ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት መቅረብ አለበት::

2. ፍቃድ ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፍቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ ዓመት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት::

3. ጽ/ቤቱ ባለሃብቱ የፕሮጀክት ግንባታዉን ሊጀምር ወይም ሊያጠናቅቅ ያልቻለዉ በበቂ ምክኒያት መሆኑን ሲያምንበት ፍቃዱን ያድሳል::

## 17 ፍቃድን ስለ ማገድ ወይም ስለ መሰረዝ

1. ባለሃብቱ ይህንን አዋጅ ወይም የኢንቨስትመንትን አዋጅ እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃ እስኪወስድ ድረስ ጽ/ቤቱ ፍቃዱን ሊያግድበት ይችላል::

2. ጽ/ቤቱ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱን በተጨባጭ ሲያረጋግጥ ፍቃዱን ሊሰርዘዉ ይችላል:-
ሀ/ ባለሃብቱ ፍቃዱን ያገኘዉ በማታለል ወይም የሃሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፣
ለ/ ባለሃብቱ ከህግ ዉጪ ፍቃዱን ለሌላ ሰዉ ካስተላለፈ ፣
ሐ/ ባለሃብቱ ፍቃዱን ያላደሰ እንደሆነና ፣
መ/ የተሰጠዉ ማበረታቻ ከታቀደላቸዉ አላማ ዉጪ ዉሎ ወይም ከህግ ዉጪ ለሌላ ሰዉ ተላልፎ ከተገኘ ይሆናል::

3. በጽ/ቤቱ የፍቃድ እገዳ ወይም ስረዛ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ምክኒያቱ ለባለ ሐብቱ በጽሁፍ መገለፅ አለበት ባለሃብቱ አስተያየቱን እንዲያቀርብ የአንድ ወር ጊዜ ይሰጠዋል::

4. ባለ ሀብቱ አስተያየቱን ካልሰጠ ወይም የተሰጠዉ አስተያየት በሚመለከተዉ

www.chilot.me

አካል ታይቶ አጥጋቢ ካልሆነ ፍቃዱ የማገድ ወይም የመሰረዝ እርምጃ ይወሰዳል።

5. ፍቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት ፍቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረዉን ጥቅም ይቋረጥበታል።

6. ከጽ/ቤቱ በስተቀር ፍቃድ በሌላ በማንኛዉም አካል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ አይችልም።

7. ፍቃዱ የጠፋበት የተበላሸበትና ፍቃድ ለማስተላለፍ ፍቃዱን ለተመዘገበበት ጽ/ቤት በማመልከት ምትክ ወይም አዲስ ፍቃድ ሊሰጠዉ ይችላል ሆኖም፦

ሀ/ የጋዜጣ ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ መዉጣት ይኖርበታል።

ለ/ በአንድ ወር ዉስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ የደንቡ ክፍያ ከተከፈለ በኃላ ምትክ ፍቃድ ይሰ ጠዋል።

ሐ/ የተበላሸዉ ፍቃድ ለጽ/ቤቱ ሊመለስ ይገባል።

መ/ ፍቃዱ ሲተላለፍ የቀድሞዉ ለጽ/ቤቱ ተመላሽ ያደርጋል። ለተላለፈለትም አዲስ ፍቃድ ይሰጠዋል።

## 18 ስለ አቤቱታ አቀራረብ

በፍቃድ ወይም በማበረታቻ ጥያቄ ላይ ጽ/ቤቱ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ባለ ሀብት ዉሳኔዉ በደረሰዉ በሰላሳ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን እንደአግባቡ ለቦርዱ ወይም ለኮሚቴዉ ወይም ለፌዴራል መንግስት ኢንቨስትመንት ቦርድ ማቅረብ ይችላል።

## 19 ስለ ኢንቨስትመንት ዋስትናና ጥበቃ

1. ለኢንቨስትመንት የዋለ ሃብት ለህዝብ ጥቅም ሲባልና በህግ በተደነገገዉ መሰረት ካልሆነ በስተቀር ሊወሰድ ወይም ሊወረስ አይችልም።

2. ለኢንቨስትመንት የዋለ ሐብት ለህዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ወይም ሲወረስ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሳይዘገይ መከፈል አለበት።

## 20 ስለ ማበረታቻ

በኢንቨስትመንት አዋጅ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጽ/ቤቱ የክልሉን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች በደንብና በመመሪያ መሰረት ለባለሀብቶች ያቀርባል።

## 21 መሬት ስለ ማግኘት

1. በተፈቀደ ኢንቨስትመንት የመሬት ጥያቄ የቀረበለት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በፌዴራል መንግስትና በክልሉ ህግ መሰረት ጥያቄዉ በቀረበለት በስልሳ ቀናት ዉስጥ የተጠየቀዉን መሬት በጽ/ቤቱ በኩል ለባለሀብቱ ያስረክባል።

2. የክልሉ መስተዳድር ለአገልግሎት ተግባር የሚዉል መሬት በመመደብ የመደባቸዉን መሬቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን ለጽ/ቤቱ ያስተላልፋል።

# ክፍል አምስት

# ልዩልዩ ድንጋጌዎች

## 22 የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ አዋጅ በወጣበት የበጀት ዓመት በህጉ መሠረት የተሰጠ ወይም የታደሰ ፍቃድ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጠ ይቆጠራል።
2. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈቀደ ኢንቨስትመንቶች የሚሰጡ ማበረታቻዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል።
3. ማንኛዉም ፍቃድ ይህ አዋጅ በወጣበት ዕለት ፍቃዱ በተሰጠበት ህግ መሰረት ሊታደስ የሚችል ከሆነ በዚህ አዋጅ መሰረት ይታደሳል።

## 23 ቅጣት

በዚህ አዋጅ ልዩልዩ አንቀጾች ጽ/ቤቱ የሚወስዳቸዉ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉዳዩ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ባለዉ ህግ ይቀጣል።

## 24 ደንብ የማዉጣት ሥልጣን

ኮሚቴዉ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊዉን ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## 25 የኢንቨስትመንት አዋጅ ተፈፃሚነት

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ሁሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## 26 የተሻሩ ህጎች

ኢንቨስትመንት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 2/88 አንቀፅ 4 /2/ እና አንቀፅ 23 ሥር የተደነገጉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

## 27 ስለ ሚቃረኑ ህግች

ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸዉም አዋጅ ፣ ደንብ ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም።

## 28 አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

6ኛ ዓመት ቁጥር 5
6th Year No. 5

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993
HARAR JULY 25/ 2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| የአንዱ ዋጋ ብር 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 26/1993 ዓም
የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ገጽ 238
የዉሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የውሀ ታሪፍ ማሻሻያ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 4/1993 ዓ.ም. . . ገጽ 242/3

## አዋጅ ቁጥር 26/1993 ዓም
## የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

**1 አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2 ማሻሻያ**

ክልሉ ዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/992 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል።

1. የማሻሻያ አዋጅ አንቀፅ 9 ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀፅ 9 ተተክቷል።

"9. የቦርዱ አደረጃጀት

www.chilot.me

1. ቦርዱ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፣ ባለሥልጣኑም በዚሁ የሥራ አመራር ቦርድ ይመራል።
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።
3. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ይወሰናል።
4. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት አበል በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወሰናል።
5. የቦርዱ አባላት ስብጥር ከሚከተሉት አካላት ይሆናሉ።

ሀ/ የክልሉ ፕሬዝዳንት——— ሰብሳቢ

ለ/ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሐላፊ—.....አባል

ሐ/የዉ/ማ/ኢ/ቢሮ ኃላፊ——— አባል

መ/የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም——— አባል

ሠ/በሀረር ከተማ የሚገኙ ጤና ተቋማት የሚወክል ባለሞያ——— አባል

ረ/ከሐረር ከተማ ነዋሪ ህዝብ የሚወክል ሁለት ተወካዮች——— አባላት

ሰ/ የሐረር ከተማ ንግድ ህብረተሰብ ተወካይ——— አባል

ሸ/ከባለሥልጣኑ ሰራተኞች የሞያ መህበር ——— አባል

ቀ/የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ድምፅ የሌለዉ የቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል።"

2. በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 11 ስር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ /3/ እና /4/ ተጨምሯል።

"3. የተዘረጉ የዉኃ መስመሮች በሊዝ በያዘዉ ወይም በሚጠቀሙበት ንብረት ላይ ማለፉን እንዲያዉቅ የተደረገ የሊዝ ያዥ ወይም ሌላ ሀጋዊ ተቃዋሚ እንደንብረቱ ባለቤት ሆኖ የተዘረጉ መስመሮችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት።"

"4 ማንኛዉም ባለንብረት፣ ባለይዞታ ወይም በሊዝ ያዥ ባለስልጣኑ መስመርቶችን ለመዘርጋት ለመጠቀም፣ ለመቆጣጠር፣ ለመንከባከብ ወይም ለመጠገን የሚካሂደዉን ሥራ ማደናቀፍ የለበትም ወይም አይችልም።"

3. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዞ በሚከተሊዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተተክቷል።

"2. ባለስልጣኑ በአገልግሎት ክልሉ ዉስጥ የዉሃ እና ፍሳሽ ሥራዎችን የሚገነባዉ ወይም የሚዘረጋዉ የከተማን መሪ ፕላን በመከተል ይሆናል።"

4. በማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 16 ሥር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 ተጨምሮበታል።

"6. ለከተማዉ ህብረተሰብ ዉኃ አቅርቦት የሚረዱ በሥሩ የሚገኙትን ነባር የዉሃ መገኛ ሥፍራዎችን እና መሥመሮችን ለመጠገን፣ የማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የዉሃ ተቋማት የማጥናትና የመገንባት።

7. በአገልግሎት ክልሉ የፍሳሽ መሥመሮችን የመዘርጋት፣ የማደስ፣ የመጠገን ፣ የማሻሻል እንዲሁም ወደ ፍሳሽ መስመሩ የሚገባዉን የፍሻሽ አይነት መጠን የመወሰን፣ ከዚሁ ጋር የተያያዙ የጤናማነት ደረጃዎችንና መመዘኛዎችን የመጠበቅና የመተግበር"



www.chilot.me

5. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 19 ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀፅ 19 ተተክቷል፡፡

"19. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ መደበኛ የሆነ ወርሃዊ ስብሳባ ይኖረወል ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስብሰባዉ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ ዉሳኔ የሚያሳልፈዉ በስብሰባዉ በተገኘ አባላት ድምፅ ብልጫ ይሆናል ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል ከሆነ ወይም የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወደ አለበት ወገን ያለዉ ሃሳብ የቦርዱ ዉሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡
4. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ቦርዱ ዝርዝር የስብሰባዉ ሥነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

6. በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 20 ስር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ /12/ /13/ እና /14/ ተጨምሯል፡፡

"12. ቦርዱ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ይከታተላል፡፡

13. የባለሥልጣኑን መዋቅርና ደሞዝ እንደአስፈላጊነቱ አስጠንቶ ያፀድቃል፡፡

14. የባለሥልጣኑን የአገልግሎት ታሪፍ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜዉ አስጠንቶ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያፀድቃል፡፡"

7. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 22 ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀፅ 22 ተተክተዋል፡፡

"22. <u>የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት፦</u>

1. የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የባለሥልጣኑን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና አስተዳደር ለማከናወን ኃላፊና ተጠሪ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉትን ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

ሀ/ በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 16 እና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 ሥር የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፡፡

ለ/ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል ይመራል ይቆጣጠራል፡፡

ሐ/ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረገዉ ግንኙነት እንዲሁም ባለሥልጣኑ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ወቅት ባለሥልጣኑን ይወክላል፡፡

መ/በቦርዱ መፅደቅ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑን የሥራ ኃላፊዎች በባለሥልጣኑ መተዳድሪያ ደንብ መሰረት የመቅጠር፣ የመመደብ የሥራ ዝርዝራቸዉን የመግለፅ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ የመዉሰድ፣

ከሥራ የማሰናበት... ወ.ዘ.ተ. ያከናዉናል።

ሠ/ በአዋጅ ቁጥር 42/1985 መሰረትና በቦርዱ በሚወጡት መተዳደሪያ ደንቦች መሰረት ሌሎች የባለሥልጣኑን ሰራተኞች የመቅጠር የመመደብ የማሳደግ የሥራ ዝርዝራቸዉን የመግለፅ ፣ እርምጃ የመዉሰድ ከሥራ የማሰናበትና ሌሎች አስተዳደራዊ ተግባሮችን ያከናዉናል።

ረ/ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ በቅማረብ ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያዉላል ይቆጣጠራል።

ሰ/ የባለሥልጣኑን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

ሸ/ የባለሥልጣኑን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል በአግባቡ እንዲያዝም ይቆጣጠራል።

ቀ/ ለባለሥልጣኑ ሥራ አፈፃጸም ቀልጣፋ የሆኑ የዉስጥ ደንቦች መመሪያዎችንና የሥራ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል በቦርዱ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያዉላል አፈፃጸማቸዉን ይቆጣጠራል።"

8. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30፣ 31፣ 32፣ 33 እና 34 እንደቅደም ተከተላቸዉ አንቀፅ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23፣ 24፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30፣ 31፣ 32፣ 33 እና 34 ሆነዋል።

3 <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም
ሐረር
ፉአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

## <u>የሐሪሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 4/1993</u>
## <u>የዉሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የዉሀ የታሪፍ ማሻሻያ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ደንብ ቁጥር 4/1993</u>

በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 10 እና በክልሉ የዉሀና ፍሳሽ አገልልሉት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15 /1991 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ይህን ደንብ አዉጥቷል ።

1. <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ ደንብ "የውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የውሀ ታሪፍ ማሻሻያ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 4/1993" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

የሐረር ከተማ የዉሃ አቅርቦት ታሪፍን በመቀየር የሐረር ከተማ ዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ደረጃ በደረጃ አገልግሎት የመስጠት አቅሙን አዳብሮ ከድጎማ ለማላቀቅ የሚረዳ በትሮፒክስ ኮንሰልቲንግ ኢንጅነርስ አማይነት ጥናቱን ቀርቦ ህብረተሰቡ እንዲያቀዉ ተደርጓል። በዚህ መሠረት

**OPTION 1 <u>FULL COST RECOVERY</u>**

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.15 |
| 1st band | $0\text{-}5m^3$ | Birr 2.25 |
| 2nd band | 6-10m˙ | Birr 4.05 |
| 3rd band | $11\text{-}30m^3$ | Birr 6.08 |
| 4th band | $>30m^3$ | Birr 12.69 |

**OPTION 2 <u>DEPRECLATION & OPERATION & MAINTENANCE COST RECOVERY</u>**

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.15 |
| 1st band | $0\text{-}5m^3$ | Birr 2.15 |
| 2nd band | $6\text{-}10m^3$ | Birr 2.25 |
| 3rd band | $11\text{-}30m^3$ | Birr 4.05 |
| 4th band | $>30m^3$ | Birr 2.50 |

**OPTION 3 <u>OPERATION & MAINTENANCE COST RECOERY</u>**

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.00 |
| 1st band | $0\text{-}5m^3$ | Birr 1.25 |
| 2nd band | $6\text{-}10m^3$ | Birr 1.60 |
| 3rd band | $11\text{-}30m^3$ | Birr 2.00 |
| 4th band | $>30m^3$ | Birr 2.50 |

የሚሉ አማራጮች ቀርበዉ ከህብረተሰቡ የመክፈል አቅሙ እና የመ/ቤቱ ደረጃ በደረጃ በገቢዉ እንዲተዳደር ማድረግ ይቻል ዘንድ በሶስተኛ አማራጭነት የቀረበዉ ታሪፍ ማለትም:-

**OPTION 3 OPERATION & MAINTENANCE COST RECOERY**

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.00 |
| 1st band | 0-5m³ | Birr 1.25 |
| 2nd band | 6-10m³ | Birr 1.60 |
| 3rd band | 11-30m³ | Birr 2.00 |
| 4th band | >30m³ | Birr 2.50 |

ተቀባይነት አግኝቶ በክልሉ ም/ቤት ፀድቋል::

## 3. የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ::

## 4. ቅጣት

በዚህ ደንብ የተወሰነውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ይቀጣል ::

## 5. ደንቡ የሚጸናበት ግዜ

ይህ ደንብ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ::

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሒም

የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት

6ኛ ዓመት ቁጥር 6
6th Year No. 6

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993
HARAR JULY 25/2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| የአንዱ ዋጋ ብር 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 27/1993
የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 27/1993. . . . . . . . . . . . . . . ገጽ244

## አዋጅ ቁጥር 27/1993 ዓ.ም የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ዉስጥ ፍትህን በማስከበርና ሠላምና ጸጥታን በማረጋገጥ ረገድ ከመስተዳድሩ የፍትህ አካላት ጋር ተጋግዞ የሚሰራ እና ህዝቡ ያገኛቸዉን መብቶችና ጥቅሞች በአመፅ ለመንጠቅ የሚደረገዉን ማንኛዉንም እንቅስቃሴ የሚከላከል የሚሊሺያ ኃይል በህዝብ ተሳትፎ ማደራጀት በማስፈለጉ፣ የሚደራጀዉ የሚሊሺያ ኃይል የሚተዳደርበትን ሁኔታ በዝርዝር መወሰንና የሚሊሺያ ኃይሉን የሚያደራጅ የሚያስተባብርና የሚቆጣጠር አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ መሠረት ከዚህ የሚከተለዉ ታዉጇል።

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

### 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 27/1993 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

www.chilot.me

## 2 ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር :-

1. "ሚሊሺያ" ማለት፡- በልዩ ሁኔታ አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ከምርት ተግባሩ ወይም ከመደበኛ ሥራው ሳይነጠል በመስተዳደሩ ወይም በግሉ በታጠቀው የጦር መሳሪያ ፀጥታ ለማስከበር በቀበሌው ነዋሪ ህዝብ የተመረጠና የደመወዝ ክፍያ የማይከፈለው ሰው ነው።
2. "ክልል" ማለት በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 2 መሰረት የተቋቋመው የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ነው።
3. "ምክር ቤት" ማለት፡- የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነው።
4. "ኮሚቴ" ማለት፡- የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነው።
5. "ኃላፊ" ማለት ፡- የክልሉ የሚሊሺያ ጽ/ቤት ዋና ኃላፊ ነው።
6. "ደንብ" ማለት፡- እንደ አስፈላጊነቱ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚወጣው ደንብ ነው።
7. "ሰው" ማለት፡- የተፈጥሮ ሰው ወይንም ህጋዊ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
8. "ሐይል" ማለት፡- የታጠቀ የሚሊሺያ ሐይል ሲሆን ከሁለት በላይ ጋንታ ይኖረዋል ወይም ይይዛል።
9. "ጋንታ" ማለት፡- ከሀይል በታች ያለ አካል ሲሆን ከሀያ ያላነሰ ሚሊሺያ የሚይዝ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት
# የሚሊሺያ ጽ/ቤት
# መቋቋም ፣ ዓላማ ፣
# አደረጃጀትና ተጠሪነት

## ክፍል አንድ
## ስለ ሚሊሺያ ጽ/ቤት
## መቋቋምና ዓላማ

### 3 ስለ ጽ/ቤቱ መቋቋም

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ ጽ/ቤት እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

### 4 የጽ/ቤቱ ዓላማ

ጽ/ቤቱ የሚከተለው ዓላማ ይኖረዋል፡- የክልሉ ነዋሪ ህዝብ የሚሊሺያ ኃይል አደራጅቶ ሰላምና ፀጥታን በማስከበር ረገድ ተሳትፎ እንዲያደርግ የማስተባበርና የሚሊሺያ ኃይልን የመምራት ዓላማ ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት
## የሚሊሺያ ጽ/ቤት አደረጃጀትና
## ተጠሪነት

### 5 የጽ/ቤት አደረጃጀት

1. ጽ/ቤት
   ሀ/ የክልል ጽ/ቤት
   ለ/ በደንቡ መሰረት በየአስተዳደር እርከኑ የሚዋቀር ሐይልና ጋንታ ይኖረዋል ዝርዝሩ በደንቡ ይወሰናል።
   ሐ/ በየቀበሌው የሚደራጅና በሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰየም ሰብሳቢ የሚመራ ከ3 ያላነሱ አባላት ያሉት የቀበሌ ሚሊሺያ ኃይል ኮሚቴ ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ አንድ /ሀ/ የተመለከተው ጽ/ቤት ኃላፊ

ከሚሰበርና መረጃ ክፍል እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችና የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል።

6 <u>ተጠሪነት</u>

1- ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለኮሚቴው ይሆናል፡

2- እያንዳንዱ የቀበሌ ሚሊሺያ ኃይል ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

7 <u>አሿሿም</u>

ኃላፊው ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ በኮሚቴው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል።

## ምዕራፍ ሦስት
## የጽ/ቤቱ፣ የኃላፊና የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር

## ክፍል አንድ
## የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

8 <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

1. በየደረጃው የሚቋቋሙ ጽ/ቤቶችንና ኮሚቴዎችን ያደራጃል ያስተባብራል ፣ ይመራል፣
2. በዚህ አዋጅና ኮሚቴው በሚያወጣው ደንብ መሠረት ለሚቋቋመው ሚሊሺያ የሰው ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፣ ያስታጥቃል፣ ያሰማራል ፣ ብቃታቸውን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ሥራን በበላይነት ይመራል፣
3. በህጉ መሰረት ወንጀል እንዳይፈፀም ይከታተላል ፣ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል ከህዝባዊ ፖሊስና ከህዝቡ ጋር በመተባበር የአካባቢ ፀጥታ ኃይል ሆኖ ይሰራል፣
4. ሚሊሺያው በልዩ ሁኔታ አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ከምርት ሥራው ወይም ከመደበኛ ሥራው በሚነጥል ተግባር እንዳይሰማራ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሀገር ሰላምና ደህንነት ከሀገር መከላከያ ሰራዊት ጋር ይሰራል፣
6. በሚወጣው ደንብ መሰረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንኡስ ዓንቀፅ 1 ለ እና ሐ መሰረት የሚቋቋሙትን አካላት ያስተዳድራል፣
7. ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
8. እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ሁለት
## ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

9 <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1- ጽ/ቤቱን ይመራል፣ ይወክላል፣

2- የጽ/ቤቱን እቅድ እና በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

3- የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለኮሚቴዉ በየሩብ ዓመቱ እንዲሁም ወቅቱን ጠብቆ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።


www.chilot.me

## ክፍል ሦስት
## የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር እና የሚሊሺያ ምልመላ

### 10 የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር

1. ወንጀል እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ ይከላከላል፣ ከህብረተሰቡና ከሀዝባዊ ፖሊስ ጋር በመተባበር የአካባቢዉ የፀጥታ ኃይል ሆኖ ይሰራል።
2. ወንጀል ሲፈፅም የተገኘዉን ሰዉ በህጉ መሰረት ይይዛል ወዲያዉኑ ከኤግዚቢቱና ዝርዝር ሪፖርት በአቅራቢያዉ ለሚገኝ ፖሊስ ያስረክባል።
3. በአካባቢዉ የአስተዳደርና ፍትህ አካላት የሚሰጡትን ተልዕኮዎችን ይፈፅማል
4. በሽፍተኝነትና በስርቆት የተሰማራ እንዲሁም የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም የተደራጁና ህግ የሚጥሱ ሰዎች መኖራቸዉን ሲገነዘብ በፍጥነት ለሚመለከታቸዉ አካላት ያሳዉቃል የአካባቢዉን ህብረተሰብ በማስተባበር በቁጥጥር ስር የሚዉሉበትን እርምጃ ይወስዳል።
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሃገር ሰላምና ደህንነት ከሃገር መከላከያ ሠራዊት ጋር ይሰራል።

### 11 የሚሊሺያ አባላትና ምልመላ

1. ማንኛዉም ዕድሜዉ ከአሥራ ስምንት ዓመት እስከ 40 ዓመት የሆነ ጤናማ አእምሮና አካላዊ ብቃት ያለዉ ፆታዉ ወንድ የሙያ ልዩነት ሳይደረግ በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ነዋሪ የሆነ ጥሩ ስነ-ምግባር ያለዉ ኢትዮጵያዊ በፍላጎት የሚሊሺያ አባል ሊሆን ይችላል።
2. የሚሊሺያ አባላት ምልመላ በአካባቢዉ ነዋሪዎች ቀጥታኛ ተሳትፎ የሚመረጥ ሲሆን የአፈፃጸሙ ዝርዝር ቢሮዉ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
3. ማንኛዉም የሚሊሺያ አባል የሆነ ከአባልነት የመሰናበት መብት አለዉ። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## ምዕራፍ አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12 ስለ ትጥቅ ህጋዊነት

1. በሚወጣዉ የሚሊሺያ ደንብ መሠረት ተመልምሎ የሚታጠቅ የሚሊሺያ ሠራዊት አባል ህጋዊ ታጣቂ መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ደብተር ይኖረዋል።
2. ማንኛዉም የሚሊሺያ አባል የሚይዘዉን ትጥቅ ህጋዊ በሆነ መንገድ ለተሰጠዉ ሥልጣንና ተግባር ብቻ ይገለገልበታል።
3. ማንኛዉም ሚሊሺያ በመንግስት የተሰጠዉን ትጥቅ መሸጥ፣ ሚሊሺያ ላልሆነዉ አሳልፎ መስጠት፣ መለወጥ፣ ማከራየት እና ማበላሸት በህግ ያስቀጣል።

### 13 ደንብ የማዉጣት ሥልጣን

ስለ ሚሊሺያ ምልመላና ሥልጠና ፣ ሥነ-ምግባርና ስንብት የሚመለከቱ ጉዳዮችና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ኮሚቴዉ ደንብ ያወጣል።

### 14 በጀት

የጽ/ቤቱ በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል።

www.chilot.me

15 <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም

ሐረር

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

7ኛ ዓመት ቁጥር 3
7th Year NO.3

ሐረር ጥቅምት 1/1994
Harar October 11/2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| የአንዱ ዋጋ 1.00 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር 28/1994

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 1994 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 28/1994 ........ ገጽ 256


## አዋጅ ቁጥር 28/1994 ዓ/ም

## በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1994 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ::

ለ1994 የበጀት ዓመት በክልሉ ዉስጥ የሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገዉን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52 አንቀጽ ንዑስ 2/ሠ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ፣

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን የ1994 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል::

### ክፍል 1
### ጠቅላላ

1. ይህ አዋጅ የ1994 በጀት ዓመት በጀት አዋጅ ቁጥር 28/1994 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::
2. ከሐምሌ 1/1993 ጀምሮ ሰኔ 30/1994 በሚፈጸመዉ በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ዉስጥ በክልሉ የሚገኘዉ ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚሁ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተዉ፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ለመደበኛ ወጪዎች | ብር | 44,952,290.00 |
| ለ. | ለካፒታል ወጪዎች | ብር | 31,500,000.00 |
| ሐ. | መጠባበቂያ በጀት | ብር | 2,047,710.00 |
| | ድምር | ብር | 78,500,000.00 |

/ሰባ ሰምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር/ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

www.chilot.me

3. ለፕሮፌሽናል ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደዉ መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም።
4. ለካፒታል በጀት ከተፈቀደዉ ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር አይቻልም።
5. በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅ ሆኖ ለቋሚ የመንግስት ሠራተኞች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች መመሪያ በማዉጣት የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ለመስጠት፣ የክፍያዉንም ጊዜ ለመወሰንና በዚህ አኳኋን በሚሰጠዉ ብድር ላይ በዓመቱ 12 % ወለድ እንዲያስከፍል ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ክፍል 2
## የበጀት አስተዳደር

### 6. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት ሥልጣን

ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸዉ ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸዉን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል።

1. ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸዉ ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸዉን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ታዟል።
2. የተፈቀደላቸዉ ጠቅላላ የበጀት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ መንግስት ሥር ለሚተዳደሩ ሆስፒታሎች ባለፈዉ በጀት አመት ካስገኙት ትክክለኛ ገቢ 50% /ሃምሳ በመቶ/ ሳይበልጥ ከዘመኑ የበጀት አመት ገቢያቸዉ እንደአስፈላጊነቱ ወጪ አያደረጉ እንዲሰሩበት ለመፍቀድ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዉ ሥልጣን ተሰጥቶታል።
3. የበጀት ዝዉዉር ሥልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል።

#### ሀ/ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

1. በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ ካፒታል በጀት፣
2. መደበኛ በጀት ከፈቀደለት አርዕስት /ንዑስ አርዕስት በበጀት አመቱ መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት /ንዑስ አርዕስት፣
3. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደዉ ወደ ካፒታል በጀት፣
4. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደዉ ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ፣

#### ለ/ ፋይናንስ ቢሮ

1. ከላይ በአንቀጽ 6/ሀ/ ከ1-4 ከተጠቀሰዉ በስተቀር፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አካላት ሲጠይቁ፣ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ዉስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላዉ ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ፣
2. ጉዳዩ የሚመለከተዉ የክልሉ መንግስት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግስት አካል ሥር ለአንድ አርዕስት፣ ንዑስ አርዕስት፣ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደን የካፒታል በጀት ወደ ሌላ አርዕስት፣ ንዑስ አርዕስት፣ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ፣
3. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲፈቀድ በክልሉ በመደበኛ በጀት ዉስጥ ለመጠባበቂያ ከተያዘዉ ወደ ሌሎች ወጪዎች ፣
4. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲፈቀድ ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለዉን ትራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች፣

ሐረር ጥቅምት 1 ቀን 1994 ዓ/ም
ፉአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
## የገቢ፣የዉጭ ዕርዳታና ብድር ማጠቃለያ

| | ብር | ብር |
|---|---|---|
| **ሀ/ መደበኛ ገቢ** | | |
| ቀጥታ ታክስ | 7,095,800.00 | |
| ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች | 2,233,200.00 | |
| ካፒታል ገቢ | | ------------ |
| የመደበኛ ገቢ ድምር | | 9,329,000.00 |
| **ለ/ የፌዴራል መንግስት ድጎማ** | | |
| ከግምጃ ቤት | 57,000,000.00 | |
| ከዉጭ ዕርዳታ | 4,611,000.00 | |
| ከዉጭ ብድር | 7,560,000.00 | |
| የድጎማ ድምር | | 69,171,000.00 |
| | | ------------ |
| ጠቅላላ ድምር | | 78,500,000.00 |

www.chilot.me

## በሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መንግሥት የ1994 በጀት አመት ወጪና የወጪ አሸፋፈን

1. ወጪ

ሀ/ መደበኛ ወጪ

| | |
|---|---|
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ | ብር 13,289,240.00 |
| ኢኮኖሚ አገልግሎት ዘርፍ | ብር 4,303,600.00 |
| ማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ | ብር 27,359,450.00 |
| መጠባበቂያ በጀት | ብር 2,047,710.00 |
| የመደበኛ በጀት ድምር | ብር 47,000,000.00 |

ለ/ ካፒታል ወጪ

| | |
|---|---|
| ኢኮኖሚ አገልግሎት | ብር 12,123,350.00 |
| ማህበራዊ አገልግሎት | ብር 17,662,950.00 |
| ጠቅላላ አገልግሎት | ብር 1,713,700.00 |
| የካፒታል በጀት ጠቅላላ ድምር | ብር 31,500,000.00 |
| ጠቅላላ ወጪ ድምር | ብር 78,500,000.00 |

2. የወጪ አሸፋፈን

ሀ/ የአገር ዉስጥ ገቢ

| | |
|---|---|
| የታክስ ገቢ | ብር 7,095,800.00 |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | ብር 2,233,200.00 |
| የአገር ዉስጥ ገቢ ድምር | ብር 9,329,000.00 |
| በጀት መረጃ | ብር 57,000,000.00 |
| ጠቅላላ ገቢ | ብር 66,329,000.00 |

ለ/ የዉጪ እርዳታ

| | |
|---|---|
| የጥሬ ገንዘብ እርዳታ | ብር 4,611,000.00 |
| የዉጪ እርዳታ ድምር | ብር 4,611,000.00 |

ሐ/ የዉጪ ብድር

| | |
|---|---|
| ከዉጪ ብድር | ብር 7,560,000.00 |
| የብድር ድምር | ብር 7,560,000.00 |
| የገቢ፣ የእርዳታና የብድር ጠቅላላ ድምር | ብር 78,500,000.00 |

www.chilot.me

7ኛ ዓመት ቁጥር 4
7th Year No. 4

ሐረር ጥር 23 1994
Harar January 31/2002

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 0.50 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 29/1994
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በሴክተር መ/ቤቶች፣ ህዝባዊ ድርጅቶች መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 29/1994 ዓ/ም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ገፅ 268

## አዋጅ ቁጥር 29/1994

## በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በሴክተር መ/ቤቶች፣ ህዝባዊ ድርጅቶች መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ።

ለድሬዳዋ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል በጥቅሉ መጠኑ ብር 8,197,000.00 /ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ብር/ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በሴክተር መ/ቤቶች፣ ህዝባዊ ድርጅቶች መካከል ጥር 22 ቀን 1994 ዓ/ም በሐረር ከተማ የተፈጸመ በመሆኑ፡-

ይህንን የብድር ስምምነት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጥር/23 ቀን 1994 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 26 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ እና በክልሉ ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀጽ 33 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### 1. አጭር ርዕስ

www.chilot.me

ይህ አዋጅ "ለድሬጃሬ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈፀሚያ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና ከሴክተር መ/ቤቶች ፣ ከህዝባዊ ድርጅቶች ብድር ለማግኘት የተፈፀመዉን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 29/1994 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ዉስጥ

ሀ/ "የብድር ስምምነት" ማለት በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በሴክተር መ/ቤቶች ፣ በህዝባዊ ድርጅቶች መካከል በጥር 22 ቀን 1994 ዓ/ም በሐረር ከተማ የተፈፀመዉ ሐረ1/ከድጃ ቁጥር 01 እስከ 07/ የብድር ስምምነት ነዉ።

ለ/ "ሴክተር መስሪያ ቤቶች" ማለት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር የተደራጁት የትምህርት ቢሮ፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት፣ ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤትና የፋይናንስ ቢሮ ናቸዉ።

ሐ/ "ህዝባዊ ድርጅቶች" ማለት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር፣ በራሳቸዉ በጀት የሚተዳደሩ መንግስታዊ መዋቅር ያላቸዉ አካላት ሲሆኑ እነሱም የዉሃና ፍሳሽ ባለሥልጣንና የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ናቸዉ።

## 3. የፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስ ቢሮ በብድር ስምምነቱ የተገኘዉን ብር 8,197,000.00 /ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ብር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲዉል ለማድረግ በዚህ አዋጅ እና በቢሮዉ ማቋቋሚያ አዋጅ 2/1988 አንቀጽ 13/6 መሠረት ይህ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## 4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር 23 ቀን 1994 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ጥር 23/1994 ዓ/ም

አቶ ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት

| | |
|---|---|
| 7ኛ ዓመት ቁጥር 5<br>7[th] Year No. 5 | ሐረር ጥር 23 1994<br>Harar January 31/2002 |

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 0.50 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 30/1994

ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ1994 የበጀት ዓመት የመንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 30/1994 ዓ.ም ............ ገፅ 272

## አዋጅ ቁጥር 30/1994

## ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ1994 የበጀት ዓመት የመንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 52 ንኡስ አንቀፅ 2/ሠ/ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማፅደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 26 ንኡስ አንቀፅ 2/ሀ/ እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀፅ 21 መሠረት የሚከተለውን የተጨማሪ የበጀት አዋጅ አውጇል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በ1994 የበጀት ዓመት ለመንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 30/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

www.chilot.me

2. **ስለተጨማሪ ገቢና ምንጩ**

ከፌዴራሉ የመንግስት ግምጃ ቤት እንዲሁም ከተለያዩ የእርዳታና የብድር ምንጮች ከተገኘዉ፤

ከፌዴራል መንግስት የተገኘዉ ተጨማሪ

| | |
|---|---|
| የበጀት ድጎማ | ብር 3,087,800.00 |
| ከዉጭ ብድር | ብር 3,757,900.00 |
| ከክልሉ ህዝባዊና መንግስታዊ ድርጅቶች ብድር | ብር 8,197,000.00 |
| ከክልሉ ግምጃ ቤት | ብር 3,838,800.00 |
| ጠቅላላ ድምር | ብር 18,881,500.00 |

/አሥራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የ1994 ዓ.ም ተጨማሪ በጀት ሆኖ እንዲሰራበት ፀድቋል።

3. **ስለ ወጭ ምደባ**

**ለካፒታል ወጭ**

ከዚህ አዋጅ አንቀፅ 2 ላይ የተመለከተዉ ተጨማሪ በጀት በሚከተሉት ዘርፎች ተደልድሎ የወጭ አመደዳቡ ከዚህ በታች በተገለፀዉ ዓይነት ይሆናል፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ/ ለድሬጃሬ ዉኃ ፕሮጀክት | ብር 15,123,000.00 |
| ለ/ በትምህርትና ጤና ሴክተር | ብር 3,757,900.00 |
| ጠቅላላ ድምር | ብር 18,881,500.00 |

/አሥራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር/ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

4. **ክፍያን ስለመፈፀም**

ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የክልሉ መንግስት አባላትና መስሪያ ቤቶች ክፍያ ሲጠይቁ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ከተጠቀሰዉ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል።

5. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥር 23 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ጥር 23/1994

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት



www.chilot.me

7ኛ ዓመት ቁጥር 6
7th year No 6

ሐምሌ 1/1994
Jul 8/2002

# የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA
# HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE



| የአንዱ ዋጋ 1.00 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|



## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 31/1994

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በ1995 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 31/1994 ........................................ ገጽ 272

### አዋጅ ቁጥር 31 /1995 ዓ.ም
### በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
### በ1995 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ

በ1995 የበጀት ዓመት በክልሉ ውስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሉቶች የሚያስፈልገውን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 52 ን/አንቀጽ 2/ሠ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን የ1995 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 26 ን/አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል 1
## ጠቅላላ

**አንቀጽ 1.**

ይህ አዋጅ የ1995 በጀት ዓመት በጀት አዋጅ ቁጥር 31/1995 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2.**

ከሐምሌ 1/1994 ጀምሮ ሰኔ 30/1995 በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በክልሉ መንግስት የሚገኘው ገቢ እና ከፌደራል መንግስት ለበጀት ዓመቱ ከሚላከው የበጀት ድጎማ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሉቶች ቀጥሉ እንደተመለከተው ፤

*ሀ. ለመደበኛ ወጪዎች ብር 56502930*
*ለ. ለካፒታል ወጪዎች ብር 36098500*
*ሐ. መጠባበቂያ በጀት ብር 4018570*
*መ. ለመንግስት እዳ ክፍያ ብር 4380000*

*ድምር ብር101000000*

/አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ብር/ ለክልሉ መንግስት ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

www.chilot.me

**አንቀጽ 3** ለፕሮፌስሽንና ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኪያ የተፈቀደውን መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም::

**አንቀጽ 4.**

ለካፒታል በጀት ከተፈቀደው ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር አይቻልም::

**አንቀጽ 5.**

በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅ ሆኖ ለቋሚ የመንግስት ሠራተኞች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች መመሪያ በማውጣት የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ለመስጠት ፣ የክፍያውንም ጊዜ ለመወሰንና በዚህ አኳኋን በሚሰጠው ብድር ላይ በዓመቱ 12 % ወለድ እንዲያስከፍል ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

## ክፍል 2

## የበጀት አስተዳደር

**አንቀጽ 6.**

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት ሥልጣን፤

ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸውን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከቤሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል::

1. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸውን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከክልሉ ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ታዟል::
2. የተፈቀደላቸው ጠቅላላ የበጀት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ መንግስት ሥር ለሚተዳደሩ ሆስፒታሎች ባለፈው በጀት አመት ካገኙት ትክክለኛ ገቢ 50% /ሃምሳ በመቶ/ ሳይበልጥ ከዘመኑ የበጀት አመት ገቢያቸው እንዳስፈላጊነቱ ወጪ እያደረጉ እንዲጠቀሙበት ለመፍቀድ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊው ሥልጣን ተሰጥቶታል::
3. የበጀት ዝውውር ሥልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል፤

ሀ/ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

1. በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት አመቱ በጀት ላልተፈቀደት አዲስ የካፒታል በጀት፤
2. መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት አርዕስት /ንዑስ አርዕስት/ በበጀት አመቱ መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት/ንዑስ አርዕስት/
3. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ወደ ካፒታል በጀት፤
4. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደሞዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ፣
5. ለመጠባበቂያ ከተያዘው በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች፣
6. ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒ - ወጪ ተፈቅዶ በስራ ላይ ያልዋለውን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች

ለ ፋይናንስ ቢሮ

1. ከላይ በአንቀጽ 6ሀ ከ1- 3 ከተጠቀሰው በስተቀር፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሲጠይቁ፤ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ውስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላው ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ፤
2. ጉዳዩ የሚመለከተው የክልሉ መንግስት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግስት አካል ሥር ለአንድ አርዕስት፤ ንዑስ አርዕስት፤ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደን የካፒታል በጀት ወደ ሌላ አርዕስት፤ ንዑስ አርዕስት፤ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ

ሐምሌ 1/1994

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

8ኛ ዓመት ቁጥር 1
8th Year № 1

ሐረር መስከረም 1996
Harar September 2003

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| የአንዱ ዋጋ 1.00 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር 32/1996
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 1996 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 32/1996 ........ ገጽ 283


## አዋጅ ቁጥር 32/1996 ዓ/ም

## በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1996 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ::

በ1996 የበጀት ዓመት በክልሉ ውስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን የ1996 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 52 አንቀጽ 2/ሠ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣ ይህ አዋጅ ታውጇል::

### ክፍል 1

### ጠቅላላ

አንቀጽ 1.

ይህ አዋጅ የ1996 በጀት ዓመት አዋጅ ቁጥር 32/1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

አንቀጽ 2.

ከሐምሌ 1/1995 ጀምሮ ሰኔ 30/1996 በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በክልሉ የሚገኘው ገቢ እና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው መንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሉ እንደተመለከተው ፤

ሀ. ለመደበኛ ወጪዎች ብር 58,841,100.00

ለ. ለካፒታል ወጪዎች ብር 27,769,180.00

ሐ. መጠባበቂያ በጀት ብር 5,109,720.00

ድምር ብር 91,720,000.00

(ዘጠና አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀያ ሺህ ብር/ ለክልሉ መንግስት ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል::

www.chilot.me

አንቀጽ 3

ለፕሮፌሽናል ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኪጃ የተፈቀደው መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም።

አንቀጽ 4.

ለካፒታል በጀት ከተፈቀደው ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር አይቻልም።

አንቀጽ 5.

በየወሩ ሳይቋረጥ እየተከፈለ የሚያልቅ ሆኖ ለቋሚ የመንግስት ሠራተኞች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች መመሪያ በማውጣት የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ለመስጠት ፤ የክፍያውንም ጊዜ ለመወሰንና በዚሁ አኳኋን በሚሰጠው ብድር ላይ በየዓመቱ 12 % ወለድ እንዲያስከፍል ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ክፍል 2

## የበጀት አስተዳደር

አንቀጽ 6.

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አካላት ሥልጣን፤

1. ክልላዊ መንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየቢሮዎቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚሁ አዋጅ የተፈቀደላቸውን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፈል ታዟል።
2. የበጀት ዝውውር ሥልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል፤

### ሀ. የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

1. በጀት ተፈቅዶለት በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት አመቱ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ የካፒታል በጀት፤
2. መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት አርዕስት /ንዑስ አርዕስት በበጀት አመቱ መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት/ንዑስ አርዕስት
3. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ወደ ካፒታል በጀት፤
4. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ
5. ለመጠባበቂያ ከተያዘው በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች
6. ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለውን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች

### ለ. ፋይናንስ ቢሮ

1. ከላይ በአንቀጽ 6ሀ ከ1 - 2 ከተጠቀሰው በስተቀር፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሲጠይቁ፤ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ውስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላው ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ፤

1.1. ጉዳዩ የሚመለከተው የክልሉ መንግስት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግስት አካል ሥር ለአንድ አርዕስት፤ ንዑስ አርዕስት፤ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደውን የካፒታል በጀት ወደ ሌላ አርዕስት፤ ንዑስ አርዕስት፤ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ

1.2. በሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ በክልሉ በመደበኛ በጀት ውስጥ ለመጠባበቂያ ከተያዘው ወደ ሌሎች ወጪዎች

1.3. በሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ ለክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለውን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች፤

መስከረም [illegible] ቀን 1996 ዓ.ም

ኩቡር ሶአድ አብራሂም
የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት
ፕሬዝዳንት


www.chilot.me

8ኛ ዓመት ቁጥር 2
8th Year No. 2

ሐረር የካቲት 1996
Harar Feb. 2004

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 1.00 ብር | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 33/1996
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 1996 የበጀት አመት ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ ቁጥር 33/1996 ........................................ ገጽ 292

## አዋጅ ቁጥር 33/ 1996 ዓ/ም
## በሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት ለ1996 በጀት ዓመት
## በሐረር ከተማ ለተከሰተው የውሀ ችግር ጊዚያዊ ማቃለያ
## የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሚክራሲያዊ ሪፖብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 52 ንዑስ አንቀፅ 2/ሠ/ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማፅደቅና ሥራ ላይ የማዋሉ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፡፡

የሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግሥት ም/ቤት አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 9/1991 አንቀፅ 21 መሠረት የሚከተሉ የተጨማሪ የበጀት አዋጅ አውጇል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ በ1996 በጀት ዓመት ለመንግሥት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 33/1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ስለተጨማሪው የገቢ ምንጭ</u>

በክልሉ መንግሥት ካለፉት በጀት ዓመታት ተመላሽ በጀት

www.chilot.me

3. <u>ስለ ወጭ ምደባ</u>

በሐረር ከተማ ለተከሰተዉ ከፍተኛ የውሃ ችግር ቦቴዎች ግዢ ለማከናወን ብር 3,000,000.00 /ሦስት ሚሊዮን ብር/ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

4. <u>ክፍያ ስለመፈፀም</u>

ጉዳዩ ለሚመለከተው የክልሉ መንግሥት ውሃና ፈሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን መ/ቤት ክፍያውን ሲጠይቅ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ወጪ በማድረግ እንዲከፈል ታዟል።

5. <u>አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ 10/6/1996 ቀን 1996 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር የካቲት 10 ቀን 1996

ፉአድ ኢብራሂም

ሐረሪ ህ/ብ/ክ/መንግሥት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

*OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE*

8 ዓመት ቁጥር 3
8th Year No 3

ሐረር የካቲት 30 ቀን 1996
HARAR 10th MARCH, 2004

| ያንዱ ዋጋ ብር<br>*Unit Price Br.* 2.00 | የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O.Box - 272. |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 34/ 1996 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ---------------------------------------- ገጽ 294

## አዋጅ ቁጥር 34/ 1996

## የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ

ሐገሪቱ ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃና ከሊተማከለ ሥርዓተ መንግሥት አወቃቀር ጋር የተጣጣመ የሐረሪ ክልል መንግሥት ሠራተኞች የሚተዳደሩበት ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቀልጣፋ፣ ገለልተኛ፣ ውጤታማ፣ ቀጣይነት እና የአሠራር ግልጽነት ያለውና የልማት አጋዥ እንዲሆን የሰው ኃይል አስተዳደሩን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የክልሉ መንግሥት ብቃት ያላቸውንና የተገሊጋዩን ህዝብ ፍላጎት በማርካት ዝንባሌ ያላቸው ባለሙያዎችን ለመሳብና በሥራ ላይ ለማቆየት፣ የሚያስችለው ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ዋስትና ስለሚያገኙበትና ስለ ሚጠበቁላቸው ተገቢ የሥራ ሁኔታዎች እንዲሁም መወጣት ስላለባቸው ግዴታዎች በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የዝውውር፣ የደመወዝ ጭማሪና የሥልጠና አፈፃፀም በሠራተኛው የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ችሎታ መዪ ልምድና የሥራ አፈፃፀም ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የደመወዝ ክፍያ በሥራ ምደባ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በማድረግ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ የሚለውን መርህ ማስጠበቅ እንደሚገባ በመታመኑ፣

የመንግሥት ሠራተኞች ተገቢ ዳኝነት የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26/2/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ አዋጅ «የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 34/ 1996» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. «የመንግሥት ሠራተኛ» ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፣ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፣

www.chilot.me

ሀ. የጽህፈት ቤት ኃላፊዎች፣ የቢሮ ኃላፊዎችና ከዚያ በላይ የሆኑ ተሿሚዎችን እንዲሁም በየደረጃው በሚገኙ /በሚቋቋሙ/ የአስተዳደር እርከኖች የሚሾሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ባለሥልጣኖች፤

ለ. የክልሉ ፍርድ ቤት ዳኞችንና አቃቢያነ ሕግን፤

ሐ. የክልሉ ፖሊስ አባሎችንና እንዲሁም በፖሊስ ደንብ የሚተዳደሩ ሌሎች ሠራተኞችን፤

መ. አግባብ ባለው ሌላ ሕግ በዚህ አዋጅ እንዳይሸፈን የተደረጉ መሥሪያ ቤትሠራተኞችን፤

2. «የመንግሥት መሥሪያ ቤት» ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመ እና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ወይም በሌላ አግባብ ባለው ሕግ በዚህ አዋጅ እንዲሸፈን የተደረገ የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ነው።

3. «የሥራ መደብ» ማለት በአንድ የመንግሥት ሠራተኛ ሙሉ የሥራ ጊዜ እንዲከናወኑ የታቀዱ ዝምድና ያላቸው ተግባሮች ስብስብ ነው።

4. «የደረጃ ዕድገት» ማለት የመንግሥት ሠራተኛን ከያዘው የሥራ ደረጃ ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ ማሳደግ ነው።

5. «ኮሚሽን» ወይም «ኮሚሽነር» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው።

6. «የበላይ ኃላፊ» ማለት የመንግሥትን መሥሪያቤት

ሀ/ በበላይነት የሚመራ ወይም

ለ/ ምክትሉ ወይም

ሐ/ ህጋዊ ውክልና የተሰጠው ነው።

7. «የሕክምና ማስረጃ» ማለት አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፍቃድ ከተሰጠው የህክምና ተቋም ስለ መንግሥት ሠራተኛ የጤና ሁኔታ የሚሰጥ የሕክምና ምስክር ወረቀት ነው።

8. «ደመወዝ» ማለት ለአንድ የሥራ መደብ የተወሰነ መነሻ ክፍያና በየጊዜው የሚሰጥ ጭማሪ ነው።

9. «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ነው።

10. «ሥራ አስፈፃሚ» ማለት በክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።

11. «ፍርድ ቤት» ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተቋቋመው የክልሉ መንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው።

## ክፍል ሁለት

## የሥራ ምደባ፣ የደመወዝ ስኬልና የአበል ክፍያ

### 3. የሥራዎች አመዳደብ

1. አንድ የሥራ መደብ ከአገልግሎቱ ዓይነት፣ ተግባር፣ ከሙያው ወይም ከሥራው ዘርፍ፣ ከሥራው ክባድነትና ውስብስብነት ካለበት ኃላፊነቶች፣ ከሚጠይቀው ትምህርት፣ ልምድና ዕውቀት፣ ችሎታና ክህሎት አንፃር እየተመዘነ በክፍለ ሥራና በደረጃ ይመደባል።

2. አንድ የሥራ መደብ

ሀ. የመጀመሪያው ምደባ ስህተት ሆኖ ሲገኝ፤

ለ. ምደባውን ለመለወጥ በቂ የሆነና ቀደም ሲል ያልተገለፀ አዲስ መረጃ ሲቀርብ ወይም፤

ሐ. በመሥሪያቤቱ አቋም መሻሻል ወይም በአሠራር ለውጥ ምክንያት የሥራ መደቡ ተግባርና ኃላፊነት ሲለወጥ እንደገና ይመደባል።

3. በሠራተኛ የተያዘ የሥራ መደብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት እንደገና ሲመደብ፦

ሀ. ከፍ ባለ ደረጃ ከተመደበና ሠራተኛው የሚጠየቀውን ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟላ ከሆነ የደረጃው ዕድገቱ ይሰጠዋል።

ለ. ዝቅ ባለ ደረጃ ከተመደበ ወይም ከፍ ባለ ደረጃ ተመድቦ ሠራተኛው የሚጠይቀውን ተፈላጊ ችሎታ የማያሟላ ከሆነ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 የንዑስ አንቀጽ /7/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

4 ባልተመደበ የሥራ መደብ ላይ ሠራተኛ መቅጠር፣ ማሳደግ፣ ማዛወር ወይም ከደረጃ ዝቅ አድርጎ መመደብ አይፈቀድም

### 4. የኮሚሽኑና የመንግሥት መሥሪያቤቶች ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽኑ

ሀ. በመንግሥት መሥሪያቤቶች የሚገኙ የሥራ መደቦች የሚመደቡባቸውን ክፍለ ሥራዎችና ደረጃዎች እንዲሁም ለእያንዳንዱ ክፍለ ሥራ የሚጠየቀውን ተፈላጊ ችሎታ ይወስናል።

ለ. ለእያንዳንዱ ክፍለ ሥራ የክፍለ ሥራ መግለጫ ያዘጋጃል።

ሐ. የመንግሥት መሥሪያቤቶችን አደረጃጀትና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 /ለ/ የሚቀርብለትን የሥራ ምደባ መጠይቅ መሠረት በማድረግ የሥራ መደቦችን በክፍለ ሥራና በደረጃ ይመደባል፤ ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል።

መ. በሥራ መደቦች አመዳደብ ላይ በመንግሥት መሥሪያቤቶችና በመንግሥት ሠራተኞች የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል።

ሠ. የሥራ መደቦች አመዳደብ መመሪያ ያወጣል።

2. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት

ሀ. አደረጃጀቱን አጥንቶ ለኮሚሽኑ አቅርቦ ያስፈቅዳል፤

ለ. መዋቅሩን መሠረት በማድረግና ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የእያንዳንዱን የሥራ መደብ ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር በመሙላት ለኮሚሽኑ አቅርቦ ያስመድባል።

ሐ. በኮሚሽኑ የተሰጠው ምደባ በሥራ ላይ እንዲውል ከመደረጉ በፊት አስተያየቱን ሊሰጥ ይችላል።

መ. በኮሚሽኑ የተሰጠው የመጨረሻ ምደባ በትክክል ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

www.chilot.me

5. ስለ ደመወዝ ስኬል

1. ኮሚሽኑ ለመንግሥት ሠራተኞች የሚያገለግሉ የደመወዝ ስኬሎችን አጥንቶ ለሥራ አስፈፃሚ ውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቅድም አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል።

2. የደመወዝ ስኬሉም ለእያንዳንዱ የሥራ ደረጃ መነሻና መድረሻ ደመወዝ እንዲሁም በየጊዜው የሚደረገውን የደመወዝ ጭማሪ የሚያመለክቱ እርከኖች ይኖሩታል።

3. ኮሚሽኑ በየጊዜው የሚከሰቱ የኢኮኖሚ ለውጦችንና ሌሎች ሁኔታዎችን ያገናዘበ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ጥናት እያካሄደ እንደአግባቡ በየአምስት አመቱ ለሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል።

6. ለእኩል ሥራ እኩል ደመወዝ ስለመክፈል

እኩል ዋጋ ያላቸው መደቦች እኩል መነሻ ደመወዝ ይኖራቸዋል።

7. የደመወዝ ክፍያ

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያቤት በየወሩ መጨረሻ ለሠራተኞቹ ወይም ለሕጋዊ ወኪሎቻቸው የደመወዝ ክፍያ ይፈጽማል።

8. ስለ ደመወዝ ጭማሪ

1. የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ በሥራ አስፈጻሚ በሚወሰነው ጊዜ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

2. አጥጋቢ፤ ከፍተኛ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ላገኙ የመንግሥት ሠራተኞች እንደሥራ አፈፃፀም ውጤታቸው መጠኑ የተለያየ የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኙ ይደረጋል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ አጥጋቢ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ላላገኙ የመንግሥት ሠራተኛ ተፈፃሚ አይሆንም።

9. የደመወዝ ክፍያን ስለመያዝና ስለመቆረጥ

1. የማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ፤

ሀ. በሠራተኛው ስምምነት፤

ለ. በፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም፤

ሐ. በሕግ በተደነገገው፤ መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም።

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ ወይም /ሐ/ መሠረት ከሠራተኛው ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሶስተኛ አይበልጥም።

10. ስለ ልዩ ልዩ አበሎች

1. ማንኛውም አበል የሚከፈለው የመንግሥትን ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

2. ኮሚሽኑ የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያን እያጠና ለሥራ አስፈፃሚ ውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቅድም አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል።

## ክፍል ሶስት

## ስለሠራተኞች ምደባና የሥራ አፈፃፀም

## ምዕራፍ አንድ

## ሠራተኛ ስለ መምረጥና መቅጠር

11. በመንግሥት ሠራተኛነት ለመቀጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች

1. የሚከተሉት የመንግሥት ሠራተኛ ሆነው ሊቀጠሩ አይችሉም፤

ሀ. ዕድሜው ከአሥራ ስምንት አመት በታች የሆነ፤

ለ. በሕግ መሠረት ካልተሠረዘለት በስተቀር የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወንጀል ፈጽሞ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የእምነት ማጉደል፤ የስርቆት ወይም የማጭበርበር ወንጀል ፈጽሞ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተፈረደበት፤

ሐ. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ /ለ/ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ የመንግሥት ሠራተኛ ከተሰናበተበት ቀን ጀምሮ ሁለት ዓመት ከመሙላቱ በፊት።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ ድንጋጌ ቢኖርም ዕድሜያቸው ከአሥራ አራት አመት በላይ የሆናቸውን አሥራ ስምንት አመት ያልሞላቸው ወጣቶች ስለሚቀጠሩበትና ስለሥራ ሁኔታቸው ኮሚሽኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

12. ስለ ውጭ ሀገር ዜጎች ቅጥር

ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ሰው በቋሚ መንግሥት ሠራተኛነት ሊቀጠር አይችልም።

13. ክፍት የሥራ መደቦችን በሠራተኛ ስለማስያዝ

1. ክፍት የሥራ መደቦችን በሠራተኛ ማስያዝ የሚቻለው የሰው ኃይል ዕቅድን መሠረት በማድረግ በቅጥር፤ በዕድገት ወይም በዝውውር ይሆናል።

2. በብሔረሰብ፤ በፆታ፤ በሐይማኖት፤ በፖለቲካ አመለካከትና በሌላም ሁኔታ በሥራ ፈላጊዎችም ሆነ በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

3. በክፍት የሥራ መደብ ላይ ሠራተኛ የሚመደበው ለሥራ መደቡ የሚጠይቀውን ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟላና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድሮ ብልጫ ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ እና /3/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በውድድሩ ውጤታቸው እኩል ወይም ተቀራራቢ ለሆኑ ሴት አመልካቾች ቅድሚያ ይሰጣል።

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/−/4/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ከተወዳዳሪዎች መካከል ዝቅተኛውን የውድድር ማለፊያ ነጥብ ለሚያሟሉ የአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ ይሰጣል።

14. ማስታወቂያ ስለማውጣትና ለቅጥር ስለሚሰጥ ፈተና

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያቤት አዲስ የመንግሥት ሠራተኛ የሚቀጠርበት ክፍት የሥራ ቦታ ሲኖረው ማስታወቂያ በማውጣት አመልካቾችን መጋበዝ አለበት።

2. ስለማስታወቂያ አወጣጥ፤ ፈተና አዘገጃጀት አሠጣጥና ውጤት አገላለጽ ኮሚሽኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/እና/2/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ማንኛውም የመንግሥት

www.chilot.me

መሥሪያቤት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ምሩቃንን በመጋበዝ ቅጥር መፈጸም ይችላል።

15. ስለ ሕክምናና ከወንጀል ነፃ ስለመሆን የሚቀርቡ ማስረጃዎች

ፈተናውን ካለፉት መካከል ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተወዳዳሪ ተመርጦ ለአገልግሎቱ ተስማሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ ከተጠቀሱት ወንጀሎች ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይደረጋል።

16. ሠራተኛን ስለ መቅጠርና ስለቃለ መሐላ

1. የተመረጠው ዕጩ የሥራ መደቡን መጠሪያ፣ የተመደበበትን ደረጃ ደመወዙንና ሥራውን የሚጀመርበትን ቀን የሚገልጽ በአሠሪው መሥሪያቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ሠራተኛን ለመቅጠር ውክልና በተሰጠው የሥራ ኃላፊ የተፈረመ የሙከራ ቅጥር ደብዳቤ ከሚያከናውነው የሥራ መደብ ዝርዝር መግለጫ ጋር ይሰጠዋል።

2. የተቀጠረው የመንግሥት ሠራተኛ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ-መሐላ ይፈፅማል። «እኔ ---------------- በመንግሥት ሠራተኛነቴ ከሁሉም በላይ አድርጌ በእውነትና በታማኝነት ሕዝቡን ለማገልገል በማናቸውም ጊዜ ሕገ መንግሥቱንና የሀገሪቱን ሕጎች ለማክበር በሥራዬ ምክንያት ያወቅሁትን ምስጢር ለሌላ ለማንኛውም ወገን ላለመግለጽ ቃል እገባለሁ።

17. ስለ መቀጠሪያ ደመወዝ አወሳሰን

ማንኛውም አዲስ ተቀጣሪ የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል መሠረት ለሚመደብበት የሥራ መደብ የተወሰነው መነሻ ደመወዝ ይከፈለዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በኮሚሽኑ ሲፈቀድ ከመነሻው ከፍ ያለ የእርከን ደመወዝ መክፈል ይቻላል።

18. የሙከራ ጊዜ

1. የሙከራ ጊዜ አላማ፣ አዲስ የተቀጠረ የመንግሥት ሠራተኛ ስለ ሥራ አፈፃፀሙ ክትትል እየተደረገ ብቃቱን ለማረጋገጥ ይሆናል።

2. የሠራተኛው የሙከራ ጊዜ በተቀጠረበት የሥራ መደብ ላይ ለስድስት ወር ይሆናል። ሆኖም ችሎታው አጠራጣሪ ሆኖ ከተገኘ የሙከራ ጊዜውን ለተጨማሪ 3 ወር ማራዘም ይቻላል።

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ /2/ እና/4/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በሙከራ ላይ ያለ የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ በመጣ ሕመም ወይም ጉዳት ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ያልጨረሰውን የሙከራ ጊዜ ከሕመሙ ወይም ከጉዳቱ ከዳነበት ጊዜ አንስቶ እንዲጨርስ ይደረጋል።

19. ቋሚ የመግሥት ሠራተኛ ስለመሆን

1 የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ የመንግሥት ሠራተኛ ቋሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይሰጠዋል።

2 የመንግሥት መሥሪያቤቱ የሠራተኛውን የሥራ አፈፃፀም ሳይሞላ የሙከራ ጊዜው ካለፈ የሚመለከተው ኃላፊ የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ አፈፃፀም እንዲሞላለት ያደርጋል። ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ የሥራ አፈፃፀሙ ያልተሞላለት እንደሆነ ሠራተኛው ለሙከራ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ እንደሆነ ይቆጠራል።

20. ጊዜያዊ ሠራተኛ ስለመቅጠር

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያቤት ጊዜያዊ ሠራተኛ ሊቀጥር የሚችለው የዘላቂነት ባሕሪይ በሌለው ሥራ ላይ ነው፤ ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ ጊዜያዊ ሠራተኛ መቅጠር ይቻላል።

2. አንድ የመንግሥት መሥሪያቤት ከፍተኛ ባለሙያ ለሚጠይቅ ማናቸውም ክፍት የሥራ መደብ በደረጃ ዕድገት ወይም በቅጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት አለመቻሉን ሲያረጋግጥ በቅድሚያ ኮሚሽኑን በማስፈቀድ የውጭ ሀገር ዜጋ በጊዜያዊነት ሊቀጥር ይችላል።

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጊዜያዊ ሠራተኛ አቀጣጠርን በተመለከተ ኮሚሽኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

ምዕራፍ ሁለት

ስለደረጃ ዕድገት

21. የደረጃ እድገት ዓላማ

የደረጃ እድገት የሚሰጠው የመሥሪያቤቱን የሥራ ውጤት ለማሻሻል ነው።

22. ስለ ደረጃ ዕድገት አሰጣጥ

1. በዲስፕሊን ቅጣት ካልታገደ በስተቀር ማንኛውም ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ ለደረጃ ዕድገት ለመወዳደር ይችላል።

2. ኮሚሽኑ የደረጃ እድገት የሚሰጥበትን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

23. የደረጃ እድገት ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 68/10/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሐሰት ማስረጃ በማቅረብ የተገኘ ወይም ሕግን በመተላለፍ የተሰጠ የደረጃ ዕድገት በማናቸውም ጊዜ ይሰረዛል።

ምዕራፍ ሶስት

ዝውውር

24. የውስጥ ዝውውር፡-

1. አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሠራተኛውን በዚያው መሥሪያ ቤት ውስጥ በተመሳሳይ የሥራ ደረጃና ደመወዝ ከአንድ የሥራ መደብ እኩል ደረጃ ወደ አለው ሌላ ተመሳሳይ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሰራ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት በውስጥ ዝውውር ሊሞላ በሚችል ክፍት የሥራ መደብ ላይ መሥራት የሚፈልጉ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሲኖሩ ዝውውሩ በውድድር ይፈፀማል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም በመሥሪያ ቤቱ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከል ወይም አደጋው ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል አንድን የመንግሥት ሠራተኛ

www.chilot.me

ደመወዝ ሳይቀንስ ደረጃው ወይም የሥራው ዓይነት ሳይጠበቅ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ በጊዜያዊነት አዛውሮ ማሠራት ይችላል።

4. ማንኛውም ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ላይ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ሊሰራ እለመቻሉ በሐኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

ሀ. በተማሣሣይ ደረጃ ሊመደብበት የሚችል ክፍት የሥራ መደብ ካለ በያዘው ደረጃ ወይም፤

ለ. በተመሣሣይ ደረጃ ሊመደብበት የሚችል ክፍት የሥራ መደብ ከሌለና ሠራተኛው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፍቃደኛ ከሆነ ደረጃው ተቀንሶ ወደ ሚስማማው የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል።

5. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ አንድን ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የሥራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ሲደረግ የተጠባባቂነት አበል ይከፈለዋል።

6. አንድን የመንግሥት ሠራተኛ ከአንድ አመት በላይ በተጠባባቂነት ማሰራት አይፈቀድም።

7. የአንድ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ መደብ የተሠረዘ እንደሆነ በመሥሪያቤቱ ውስጥ ተመሣሣይ ደረጃ ወደ አለው የሥራ መደብ ይዛወራል።

25. ከሌላ መሥሪያ ቤት የሚደረግ ዝውውር

1. በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያቤት የሚገኝ ክፍት የሥራ መደብ ከሌላ የመንግሥት መሥሪያቤት በሚዛወር ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ እንዲያዝ የሚደረገው መሥሪያቤቱ የተዘጋ ወይም የሥራ መደቡ የተሰረዘ ከሆነና ዝውውሩን ኮሚሽኑ ሲወስን ነው።

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚዛወር የመንግሥት ሠራተኛ በያዘው የሥራ ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኘ የነበረው ደመወዝና ሌሎች መብቶቹ አይቀነሱበትም።

3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ቀጣሪው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ሠራተኛው ሲስማሙበት አንድ የቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት አንድ የተወሰነ ሥራ ለመፈፀም ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በጊዜያዊነት ተመድቦ እንዲሠራ ሊደረግ ይችላል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የተመደበ ሠራተኛ፤

ሀ. ደመወዝና ማናቸውም ጥቅሙ በምደባው ምክንያት አይጓደልበትም፤

ለ. የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቱ በአሠሪው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተሞልቶ ለቀጣሪው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይተላለፍለታል፤

ሐ. ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ የድሲፕሊን እርምጃ የሚወሰድበት በቀጣሪው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይሆናል፤

ምዕራፍ አራት

የሥራ አፈፃፀም

26. ሥራ አፈፃፀም ግምገማ፦

1. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ዓላማ፤ ሠራተኞች፤

ሀ. ሥራቸውን በሚጠበቀው መጠን፤ የጥራት ደረጃና ጊዜ በተሟላ ሁኔታ እንዲያከናውኑ፤

ለ. ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲያውቁ፤

ሐ. የወደፊት የሥራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና ለሥራ ያላቸውን ተነሳሽነት እንዲያጎለብቱ፤ ማስቻል ይሆናል።

2. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ በግልጽና ሥራው የሚመለከታቸው የመንግሥት ሠራተኞች በተገኙበት በጋራ ይከናወናል።

3. የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፀማል።

ክፍል አራት

የሥራ ሰዓትና ልዩ ልዩ ፍቃዶች

ምዕራፍ አንድ

ስለ ሥራ ሰዓት

27. መደበኛ የሥራ ሰዓት

የመንግሥት ሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት እንደየሥራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሳምንት ከ40 ሰአት መብለጥ የለበትም።

28. የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት

የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የሥራ አስፈፃሚ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

29. የትርፍ ሰዓት ሥራ

የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሠራ የመንግሥት ሠራተኛ የማካካሻ ዕረፍት ወይም የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚሰጥበት ሁኔታ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤ ሆኖም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ከሚከፈለው መጠን ያነሰ ይሆናል።

30. ስለ ሕዝብ በዓላት

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕዝብ በዓል ወይም በመንግሥት ውሣኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውሉበት ቀን ባለመሥራቱ መደበኛ የደመወዝ ክፍያው አይቀነስበትም።

2. የሥራ ሁኔታ አስገድዶ በሕዝብ በዓል ቀን እንዲሠራ የታዘዘ የመንግሥት ሠራተኛ የትርፍ ሠዓት ክፍያ ይሰጠዋል።

ምዕራፍ ሁለት

የዓመት እረፍት ፍቃድ

31. የአመት እረፍት ፍቃድ መሠረተ ሐሳብ

1. የዓመት ዕረፍት ፍቃድ የሚሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ ስተወሰነ ጊዜ በማረፍ አገልግሎቱን በታደሰ መንፈስ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው።

2. ማንኛውም አዲስ ተቀጣሪ የመንግሥት ሠራተኛ የአሥራ አንድ ወራት አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የአመት ዕረፍት ፍቃድ ለማግኘት መብት የለውም።

3. የአመት ዕረፍት ፍቃድ በገንዘብ አይለወጥም፤ ሆኖም የሠራተኛው አገልግሎት በመቋረጡ ያልተወሰደ የአመት ዕረፍት ፍቃድ በገንዘብ እንዲለወጥ ይደረጋል።

www.chilot.me

32. <u>የአመት ዕረፍት ፈቃድ ቀናት</u>

1. አንድ አመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ 20 የሥራ ቀናት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል።

2. ከአንድ አመት በላይ ያገለገለ ሠራተኛ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የአመት የዕረፍት ፈቃድ ያገኛል ሆኖም የሚሰጠው የአንድ አመት ዕረፍት ፈቃድ ከ30 የሥራ ቀኖች መብለጥ የለበትም።

3. በሌላ የመንግሥት መሥሪያቤት ቀደም ሲል የተሰጠ አገልግሎት ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ አፈፃፀም የሚታሰብ ይሆናል።

33. <u>የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ</u>

1. የአመት ዕረፍት ፈቃድ የመሥሪያ ቤቱን ዕቅድ መሠረት በማድረግና በተቻለ መጠን የሠራተኛውንም ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጀውና ሠራተኛውም እንዲያውቀው በሚደረግ ፕሮግራም መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ይሰጣል።

2. ሠራተኛው ፈቃዱን በሚወስድበት ጊዜ በዕረፍት ላይ የሚቆይበት ወር ደመወዙን በቅድሚያ ሊወስድ ይችላል።

34. <u>የዓመት የዕረፍት ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>

1. የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ምክንያት መሥሪያቤቱ ለሠራተኛው የአመት ዕረፍት ፈቃድ ፈቃዱን በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊሰጠው ያልቻለ እንደሆን የመሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ ለሁለት የበጀት አመት ሊያስተላልፈው ይችላል፤ ሆኖም ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በሶስተኛው በጀት ዓመት ለሠራተኛው መስጠት አለበት።

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 31/3/ ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የዓመት ዕረፍት ፈቃዱ ለሁለት ዓመት የተላለፈበት የመንግሥት ሠራተኛ የተላለፈውን የአመት ዕረፍት ፈቃድ ግማሹን በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

## <u>የወሊድ ፈቃድ፤ የሕመም ፈቃድና ሌሎች ፈቃዶች</u>

35. <u>የወሊድ ፈቃድ</u>

1. ነፍሰጡር የሆነች የመንግሥት ሠራተኛ፤

ሀ. ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርመራ ለማድረግ ሐኪም በሚያዘው መሠረት ደመወዝ የሚከፈለበት ፈቃድ ይሰጣታል።

ለ. ከመውለዷ በፊት ዕረፍት እንድታደርግ ሐኪም ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት እረፍት ይሰጣታል።

2. ነፍሰጡር የሆነች የመንግሥት ሠራተኛ መውለጃዋ ሲደርስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት 30 ተከታታይ ቀናት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ እንዲሁም ስትወልድ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ 60 ተከታታይ ቀናት የወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር ይሰጣታል።

3. ሠራተኛዋ የወሰደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሳያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት የምትቆይበት ዕረፍት በበጀት ዓመቱ ካላት የአመት ዕረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት ዓመቱ የአመት ዕረፍት ፈቃድ የሌላት እንደሆነ ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት የዕረፍት ፈቃዷ ይቀነሳል።

4. ሠራተኛዋ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ የተወሰነውን የወሊድ ፈቃድ ከጨረሰች በኋላ ብትታመምና ተጨማሪ ፈቃድ የሚያስፈልጋት መሆኑ በሐኪም ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 36 ወይም 37 በተደነገገው መሠረት የሕመም ፈቃድ መውሰድ ትችላለች።

36. <u>የሕመም ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕመም ምክንያት ሥራ መሥራት ያልቻለ እንደሆነ የሕመም ፈቃድ ይሰጠዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወሰድም ሕመም ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የአሥራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከስምንት ወር ወይም በአራት አመት ውስጥ ከአሥራ ሁለት ወር አይበልጥም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር፤ ለሚቀጥሉት ሶስት ወራት ከግማሽ ደመወዝ ጋር እና ለመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ያለ ደመወዝ ይሆናል።

4. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሲታመም፤

ሀ. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለመሥሪያቤቱ ማሳወቅ አለበት።

ለ. በተከታታይ ከሶስት ቀን ወይም በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከ6 ቀን በላይ በሕመም ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ለመታመሙ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

37. <u>ለጊዜያዊ ሠራተኛ ስለሚሰጥ የሕመም ፈቃድ</u>

በሕመም ምክንያት ሥራውን መሥራት ያልቻለ ጊዜያዊ የመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጠው የሕመም ፈቃድ ከመንግስት መሥሪያቤቱ ጋር በሚገባው ውል መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

38. <u>የጋብቻ ፈቃድ</u>

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሲያገባ ሶስት የሥራ ቀናት የጋብቻ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል።

39. <u>የሐዘን ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ፤ ተወላጅ፤ ወላጅ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የሶስት ተከታታይ ቀናት የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል።

2. ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከቱት ውጭ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የአንድ ቀን የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል። ሆኖም በዚህ ምክንያት የሚሰጥ የሐዘን ፈቃድ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከስድስት ቀን መብለጥ የለበትም።

**40. ከደመወዝ ጋር ስለሚሰጥ ልዩ ፍቃድ**

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ፤

1. ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት መጥሪያ ሲደርሰው የተጠራበት ጉዳይ እስከሚያበቃ ጊዜ ድረስ፤
2. በሕዝብ ምርጫ ሥልጣን የሚይዙ የመንግሥት ኃላፊዎችን ለመምረጥ ሲሆን ምርጫው ለሚወሰድበት ጊዜ ከደመወዝ ጋር ልዩ ፈቃድ ይሰጠዋል።

**41. ያለ ደመወዝ ስለሚሰጥ ልዩ ፍቃድ**

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በበቂ ምክንያት ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፍቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅና የመሥሪያቤቱን ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን የመሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊፈቅድለት ይችላል።

**42. የሕክምና አገልግሎት**

1. ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት የሕክምና ተቋሞች የሚሰጠውን ማንኛውንም የህክምና አገልግሎት በነፃ የማግኘት መብት ይኖረዋል።
2. ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛውንና አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆቹን በመንግሥት የህክምና ተቋሞች ውስጥ በግማሽ ክፍያ የማሳከም መብት ይኖረዋል።
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለሚያገኘው የህክምና አገልግሎት የሚያደርገውን የመዋጮ መጠን ኮሚሽኑ፤ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ እና የጤና ቢሮ በጋራ አጥንተው ለሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ በሚወሰነዉ ደንብ መሰረት ይፈጸማል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የሚወሰነው የመዋጮ መጠን ለሁሉም የመንግሥት ሠራተኞች እኩል ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## የሥራ አከባቢ ደህንነትና ጤንነት

**43. በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት**

1. በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት አግባብ ባለው የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ የተሰጠው ትርጓሜ ለዚህም ክፍል ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም፤ ሠራተኛው ሆን ብሎ በተለይም በመንግሥት መሥሪያቤቱ አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እጽ ለክሮ በሥራ ላይ በመገኘቱ የደረሰበት ጉዳት በሥራው ምክንያት እንደደረሰ ጉዳት አይቆጠርም።

**44. ስለ አደጋ መከላከያ እርምጃዎች፡-**

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፤
   ሀ. የሥራ ቦታው በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን የማረጋገጥ፤
   ለ. የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን ለሠራተኞች የማቅረብና ስለ አጠቃቀማቸው መመሪያ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።
2. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ፤
   ሀ. ደህንነትንና ጤንነትን ለመጠበቅ የወጡ መመሪያዎችን የማክበር፤
   ለ. የተሰጡትን አደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች በአግባቡ የመጠቀም እና
   ሐ. አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲገመት ለሚመለከተው የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

**45. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ስለሚሰጥ ሕክምናና ፍቃድ**

1. በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ የሚያስፈልገውን የሕክምና ወጪ መሥሪያቤቱ ይችላል።
2. በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስከሚመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታው መሥራት የማይችል መሆኑን በሕክምና ማስረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ የሕመም ፍቃድ ከሙሉ ደመወዙ ጋር ይሰጠዋል፤ ሆኖም የሚሰጠው የሕመም ፍቃድ በማናቸውም ሁኔታ ከ12 ወር አይበልጥም።
3. በአሥራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራ መመለስ ያልቻለ የመንግሥት ሠራተኛ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 46 የተደነገጉት ጥቅሞች ይጠበቁለታል።
4. ሠራተኛው ሕክምናውን በአግባቡ ባለ መከታተሉ ወይም በሐኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ሕክምናውን ያጓተተ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ መሠረት የሚሰጠው ሕክምናና ፍቃድ ይቋረጥበታል።

**46. ስለ ጉዳት ጡረታና ካሳ ክፍያ**

1. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን ያጣ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠው መብት ይጠበቅለታል።
2. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ዘላቂ ሙሉ የመሥራት ችሎታውን ያጣ ጊዜያዊ የመንግሥት ሠራተኛ የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መጠን የአንድ ዓመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ የሚያገኘው የክፍያ መጠን ይሆናል።
3. በጊዜያዊ የመንግሥት ሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ከፊል የመሥራት ችሎታ ማጣት ከሆነ የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተመለከተው ክፍያ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከመሥራት ችሎታ ማጣቱ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል።
4. ከባድ የአካል ወይም የመልክ መበላሸትን ያደረሰ ጉዳት የመሥራት ችሎታ ማጣትን ባያስከትልም ለዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈፃፀም እንደዘላቂ ከፊል የመሥራት ማጣት ይቆጠራል።
5. ሠራተኛው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የሞተ እንደሆነ፤
   ሀ. ሟቹ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ ከሆነ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ አበል ወይም፤

www.chilot.me

57. ፖለቲካ ተሳትፎ ገለልተኛ ስለመሆን፦

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሥራውን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋልና በዚሁ ምክንያት አድልዎ መፈፀም የለበትም።

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የመንግሥትን መደበኛ የሥራ ሰዓትና ኃላፊነቱን ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ለአባላቱ ድጋፍ ወይም ተቃውሞ በማሰባሰብ ተግባር ማዋል የተከለከለ ነው።

58. በመንግሥት ሥራና በግል ጥቅም መካከል ስለሚፈጠር ግጭት

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከራሱ ወይም ከዘመዱ ወይም ከወዳጁ ጥቅም ጋር የተያያዘና ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር ግጭት የሚፈጥርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ለአለቃው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥምና ጉዳዩ የተገለጸለት ኃላፊ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌላ የመንግሥት ሠራተኛ ተተክቶ ሥራውን እንዲያከናውን ሊያደርግ ይችላል።

59. ስለ ስጦታ

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት ሠራተኛነቱ ለሰጠው ወይም እንዲሰጥ ለሚጠበቀው ግልጋሎት ማንኛውም ዓይነት ስጦታ መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም።

60. ገቢን ስለማሳወቅ

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ አስፈላጊነቱ ታምኖበት በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሲጠየቅ ከደመወዙ ሌላ የሚያገኘውን ገቢ መግለጽ አለበት።

61. ለሕክምና ምርመራ የመቅረብ ግዴታ፦

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከኤች አይ ቪ /ኤድስ/ ምርመራ በስተቀር ከሥራው ጋር በተያያዘ በቂ ምክንያት የህክምና ምርመራ እንዲያደርግ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሲጠየቅ ለምርመራ የመቅረብ ግዴታ አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ስሚደረግ የህክምና ምርመራ የሚያስፈልገውን ወጭ የመንግሥት መሥሪያቤቱ ይችላል።

62. የንብረት አያያዝና አጠቃቀም

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለሥራው ማከናወኛ የተሰጡትን መሣሪያዎችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠበቅና የመጠቀም ኃላፊነት አለበት።

63. በዕዳ የመጠየቅ ኃላፊነት

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለሥራው ማከናወኛ በተሰጡት መሣሪያዎችና መገልገያዎች ላይ በሚደርስ ጉዳት ወይም ጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱ ወይም ጥፋቱ በሠራተኛው ቸልተኛነት ወይም ሆን ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ ነው።

## ክፍል ዘጠኝ

## የዲሲፕሊን እርምጃዎች

64. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ

የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ የመንግሥት ሠራተኛ በፈፀመው የዲስፕሊን ጉድለት ተጸጽቶ እንዲታረምና ብቁ ሠራተኛ እንዲሆን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው።

65. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓይነቶችና አመዳደብ

1. የዲሲፕሊን ጉድለት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል።

ሀ. የቃል ማስጠንቀቂያ፣

ለ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣

ሐ. እስከ አንድ ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፣

መ. እስከ ሶስት ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ

ሠ. ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ፣

ረ. ከሥራ ማሰናበት፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/–/ሐ/ የተዘረዘሩት ቀላል የዲስፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/መ/–/ረ/ የተዘረዘሩት ከባድ የዲስፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ።

66. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች

የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ።

1. ትእዛዝ ባለማክበር፤ በቸልተኝነት፤ በመስገም ወይም የአሠራር ሥነ–ሥርዓትን ባለመከተል በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤

2. ጉዳዮችን ሆን ብሎ ማዘግየት ወይም ባለጉዳዮችን ማጉላላት፤

3. ሥራ እንዳይሠራ ሆን ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

4. በቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት እርምጃዎች ባለመታረም ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከሥራ መቅረት ወይም የሥራ ሰዓት አለማክበር፤

5. በሥራ ቦታ በጠብ አጫሪነት መደባደብ፤

6. በልማዳዊ ስካር ወይም አደንዛዥ እፅ ሱስ በመመረዝ ሥራን መበደል፤

7. ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

8. በሥራ ቦታ ስሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈፀም፤

9. የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈፀም፤

10. የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀም፤

11. በመሥሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤

12. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 የተደነገገውን መተላለፍ፤

13. በሥልጣን አላግባብ መጠቀም፤

14. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይ ክብደት ያለው ሌላ የዲስፕሊን ጉድለት መፈፀም፤

www.chilot.me

67. <u>የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያቤት የሠራተኞችን የዲስፕሊን ክስ አጣርቶ የውሳኔ ሐሳብ ለሚመለከተው የሥራ ኃላፊ የሚያቀርብ የዲስፕሊን ኮሚቴ ያቋቁማል።

2. በማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ የዲስፕሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ሠራተኛው ፈጸመ የተባለውን የዲስፕሊን ጉድለት እንዲያውቀው መደረግና ራሱን የመከላከል ዕድል ሊሰጠው ይገባል።

3. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያቤቶች የሥነ-ምግባር መጣስና የሙስና ወንጀል የተፈፀመ ለመሆኑ ጥርጣሬ ሲኖረው በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ ማካሄድ ይችላል። ከከባድ የሥነ-ምግባር መጣስና በሙስና ወንጀል ጉዳይ ግን ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት በምርመራ ያገኙትን ውጤት ሥልጣን ላለው የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ወይም የሚመለከተው ህጋዊ አካል ሪፖርት የማድረጉ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ የዲስፕሊን ቅጣት ማንኛውንም የፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል።

68. ከሥራ ስለማገድ

1. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ ታግዶ መቆየት ለሥራው አፈፃፀም ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ሠራተኛውን ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ከሥራና ደመወዝ እግዶ ለማቆየት ይቻላል።

2. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በወንጀል ወይም በዲስፕሊን ጥፋት በህግ የተከሰሰ እንደሆነና ሊመሰከርበት ጥፋቱ ከሥራው የሚያስወጣው መሆኑ ሲገመት ከሥራ ታግዶ መቆየት አለበት።

69. <u>ስለ ይርጋ ጊዜ</u>

1. ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የምርመራውን ጊዜ ሳይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም።

2. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መውሰድ የሚገባውን የዲስፕሊን እርምጃ ሳይወስድ የቀረው ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል።

<u>ክፍል አሥር</u>

<u>የአስተዳደር ፍርድ ቤት</u>

70. <u>የአስተዳደር ፍርድ ቤት ስለማቋቋም</u>

1. የመንግሥት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን የሥራ ክርክር ይግባኝ አይቶ የሚወስን የአስተዳደር ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ፍርድ ቤቱ የሚቀርቡለትን የይግባኝ አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥ ችሎት ይኖረዋል።

3. ችሎቱም በኮሚሽኑ የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና ሁለት አባላት ይኖሩታል።

71. <u>በፍርድ ቤቱ ስለሚታዩ ጉዳዮች፦</u>

የመንግሥት ሠራተኛ

1. ከህግ ውጭ ከሥራ በመታገዱ ወይም አገልግሎቱ በመቋረጡ፤

2. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የተወሰነበት በመሆኑ፤

3. ከህግ ውጭ ደመወዙ ወይም ሌሎች ክፍያዎች የተያዘበት ወይም የተቆረጠበት በመሆኑ፤

4. በሥራው ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ጋር በተያያዘ መብቱ በመጓደሉ፤ ቅር በመሰኘት የሚያቀርበውን ይግባኝ ፍርድ ቤቱ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል

72. <u>የፍርድ ቤቱ ውሳኔ</u>

1. ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ከመረመረ በኋላ ውሳኔውን ለማጽናት ለመሻር ወይም ለማሻሻል ይችላል።

2. የውሳኔው ግልባጭ ለተከራካሪ ወገኖች ይሰጣል።

3. ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገር ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ሆኖም ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የህግ ክርክር ያነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

73. <u>የውሳኔ አፈፃፀም</u>

1. ማንኛውም ውሳኔ የተሰጠበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ወዲያውኑ የመፈፀም ግዴታ አለበት

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 72 መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ እስከ 30 ቀን አልተፈፀመልኝም በማለት የውሳኔው ተጠቃሚ ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን እንዲያስፈፅምለት ለክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመራለታል።

3. የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ያላስፈፀመው የመሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ በመሥሪያቤቱና በሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል።

<u>ክፍል አሥራ አንድ</u>

<u>አገልግሎት ስለማቋረጥና ስለማራዘም</u>

74. <u>በገዛ ፍቃድ ከሥራ መሰናበት</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ሥራውን በገዛ ፍቃዱ ሊለቅ ይችላል።

2. የመንግሥት ሠራተኛው ለሥራው እጅግ አስፈላጊና በቀላሉ ለመተካት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የመሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ የሥራ መልቀቂያውን ጥያቄ ከሶስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል።

75. <u>በሕመም ምክንያቱ ለአገልግሎት ብቁ አለመሆን</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 /2/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ለመመለስ ካልቻለ፤ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ በሕመም ምክንያት ለሥራው ብቁ እንዳልሆነ ተቆጥሮ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ሊደረግ ይችላል።

2. ማንኛውም ጊዜያዊ የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 መሠረት የተሰጠው የህመም ፍቃድ ጊዜ ካበቃ በኋላ ወደ ሥራው መመለስ ካልቻለ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ሊደረግ ይችላል።

www.chilot.me

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 45/2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ ለዘለቄታው መሥራት አለመቻሉ በህክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ ወዲያውኑ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል።

76. በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

1. ማንኛውም ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ የተመደበበትን ሥራ ያለውን እውቀትና ችሎታ ተጠቅሞ ለመሥራት የተቻለውን ጥረት እያደረገ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ከመካከለኛ ነጥብ በታች ከሆነ ከሥራ ማሰናበት ይቻላል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም ለተከታታይ 5 ዓመታት ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ሲያገኝ የነበረ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ በተከታታይ ለሶስት ጊዜ ከመካከለኛ ነጥብ በታች ካልሆነ በስተቀር ከሥራ አይሰናበትም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ መሠረት የመንግሥት ሠራተኛውን ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው፤

ሀ. ለያዘው የሥራ መደብ የሚያስፈልገውን ሥልጠና ፀመስጠት ወይም፤

ለ. ከዚያው የሥራ ደረጃ ጋር ተመሣሣይ በሆነና ሊሠራው ወደ ሚችለው ሌላ የሥራ መደብ በማዛወር፤ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሲሆን ቢያንስ ለአንድ ዓመት ወይም በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ሲሆን ቢያንስ ለአንድ ዓመት ተኩል እንዲሰራ ከተደረገ በኋላ ሠራተኛው የሥራ አፈፃፀም ውጤቱን ለማሻሻል ያልቻለ እንደሆነ የአንድ ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው።

77. በእሥራት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 እና 45 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ በመታሰሩ ወይም በሌሎች ከአቅሙ በላይ በሆኑ ምክንያቶች አገልግሎቱን ካቋረጠና በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራው ካልተመለሰ ከሥራ ለማሰናበት ይቻላል።

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 እና 45 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ማንኛውም ጊዜያዊ የመንግሥት ሠራተኛ በመታሰሩ ወይም ሌሎች ከአቅሙ በላይ በሆኑ ምክንያቶች እስከ አንድ ወር ወደ ሥራው ካልተመለሰ ከሥራ ማሰናበት ይቻላል።

78. ቅጥርን ስለ መሰረዝ

የሐሰት የትምህርት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማቅረብ ወይም ሥልጣን በሌለው ሰው ወይም ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን ደንብና መመሪያ ወይም ሌላ ማናቸውንም ህግ በመተላለፍ የተፈፀመ ቅጥር በመንግሥት መሥሪያቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በኮሚሽኑ ይሰረዛል።

79. ሠራተኛ ስለመቀነስ

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ፤

ሀ. የሥራ መደቡ ሲሰረዝ፤

ለ. የመንግሥት መሥሪያቤቱ ሲዘጋ፤ ወይም

ሐ. ትርፍ የሰው ኃይል ሲኖር፤

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24/7/ ወይም 25/1/ መሠረት ለማዛወር ካልተቻለ ወይም የመንግሥት ሠራተኛው ዝቅ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፍቃደኛ ካልሆነ ከሥራ ይሰናበታል።

2. በዚህ አንቀጽ 1/ሐ/ መሠረት ቅነሣ የሚደረገው የመንግሥት ሠራተኛው በተመሣሣይ የሥራ መደብ ላይ ካሉ ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ጋር ሲወዳደር በሥራ ውጤቱና ባለው ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

80. በዲሲፕሊን ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

1. ማንኛውም ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ፦

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1/2/ መሠረት የዲስፕሊን ቅጣት የተወሰነበት፤ እና

ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት ይግባኝ ብሎ ቅጣቱ ያልተሰረዘለት እንደሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል።

2. የመንግሥት ሠራተኛው የተላለፈበት የዲስፕሊን ውሳኔ በይግባኝ ከተሻሻለለት ወይም ከተሰረዘለት በክርክር ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ታስቦ ያለ ወለድ ይከፈለዋል።

3. ጊዜያዊ የመንግሥት ሠራተኛ፦

ሀ. በዲሲፕሊን ቅጣት፤ ወይም

ለ. የሥራ ውሉ ዘመን ሲፈፀም፤ ያለ ምንም ተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት ከሥራ ይሰናበታል።

81. በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ አገልግሎቱ ካልተራዘመ በቀር በህግ ከተወሰነው የመጦሪያ ዕድሜ ከደረሰበት የመጨረሻ ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለ ምንም ተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎት እንዲቋረጥ መደረግ አለበት።

2. የመንግሥት ሠራተኛው ጡረታ ከመውጣቱ ከስድስት ወር በፊት የበላይ ኃላፊው በጽሁፍ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት።

82. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ወይም ሲጠይቅ ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓይነት፤ የአገልግሎት ዘመኑ፤ ሲከፈለው የነበረው ደመወዝና ከሥራ የተሰናበተበትን ምክንያት የሚገልጽ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

83. አገልግሎት ሲቋረጥ ስለሚፈፀም ክፍያ

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 79 መሠረት በቅነሣ ምክንያት ከሥራ ከተሰናበተና የጡረታ አበል የማይከፈለው ከሆነ፤

ሀ. ለመጀመሪያ አንድ አመት የሶስት ወር ደመወዝ፤

ለ. በተጨማሪ ለአገለገለበት ለእያንዳንዱ ዓመት የወር ደመወዙ 1/3 እየታከለ ይከፈለዋል። ሆኖም የሚሰጠው ክፍያ ከሠራተኛው የ12 ወር ደመወዙ መብለጥ የለበትም።

2. የሙከራ ጊዜውን ለጨረሰና ከአንድ ዓመት በታች ላገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ የሚፈፀመው ክፍያ ከአገልግሎት ጋር እየተመዛዘነ ይታሰባል።

www.chilot.me

3. አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ በሞት ምክንያት አገልግሎቱ ሲቋረጥ፣ በህይወት ላለ ለመንግሥት መሥሪያቤቱ በጽሁፍ ላሳወቃቸው የትዳር ጓደኛው ወይም በስሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ቤተሰቦቹ የሶስት ወር ደመወዝ ይከፈላል።

84. አገልግሎት ስለማራዘም

1. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የመጦሪያ ዕድሜው ከደረሰ በኋላ በአንድ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት በጠቅላላው ከአሥር ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱን ማራዘም ይቻላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የአንድን የመንግሥት ሠራተኛ አገልግሎት ማራዘም የሚቻለው፤

ሀ. የሠራተኛው ትምህርት ልዩ እውቀትና ችሎታ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፤

ለ. በደረጃ እድገት በዝውውር ወይም በቅጥር ተተኪ ሠራተኛ ለማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤

ሐ. ሠራተኛው ለሥራው ብቁ መሆኑ በህክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

መ. ሠራተኛው አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ፤ እና

ሠ. የአገልግሎቱ መራዘም ለኮሚሽኑ ቀርቦ ሲፈቀድ፤ ነው።

85. ቅጥር የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪና ሌላ ጥቅም መሠረዝ የሚያስከትለው ውጤት፦

1. ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅም የተሰረዘበት የመንግሥት ሠራተኛ የመሰረዙ እርምጃ እስከ ተወሰደበት ጊዜ ድረስ የተከፍለውን ደመወዝና ሌሎች ጥቅሞች እንዲመልስ አይጠየቅም።

2. የተሳሳተ ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ጥቅም ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የፈቀደ የሥራ ኃላፊ ወይም የኮሚቴ አባል አግባብ ባለው የወንጀለኛ

መቅጫ ህግ ድንጋጌ መሠረት በወንጀል መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ እላአግባብ ለወጣው ወጪ ተጠያቂ ይሆናል።

86. የሥልጣን ውክልና ስለመስጠት

ኮሚሽኑ የሲቪል ሰርቪሱን አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመንግሥት መሥሪያቤቶች በውክልና ማስተላለፍ ይችላል።

87. የአዋጁን አፈፃፀም ስለ መቆጣጠር፦

1. ኮሚሽኑ ይህን አዋጅና በአዋጁም መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የመቆጣጠር ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል።

2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ በማናቸውም ጊዜ፤

ሀ. በመንግሥት መሥሪያቤቶች በመገኘት ወይም እንዲላኩለት በማዘዝ ማህደሮችንና ሌሎች መረጃዎችን መመርመር፤ እና

ለ. ጉዳዩ የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ወይም ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች በቃል ወይም በጹሑፍ እንዲያስረዱ መጠየቅ፣ ይቻላል።

3. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በሚያደርገው ምርምራ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ህግ መጣሱን ወይም አድሎዎ መፈፀሙን ከደረሰበት፣

ሀ. ትክክል ያልሆነው አሠራር እንዲስተካከል የማዘዝ፣

ለ. ጉዳዩ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ አፈፃፀሙን የማገድ፣

ሐ. ለድርጊቱ ተጠያቂ በሆነው የሥራ ኃላፊ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድበት የማድረግ፣ ሥልጣን ይኖረዋል።

## ክፍል አሥራ ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

88. ደንብና መመሪያን የማውጣት ሥልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሥራ አስፈፃሚ ሊያወጣ ይችላል።

2. ኮሚሽኑ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

89. ተፈፃሚነት

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

90. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 89 ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት ሠራተኞች ደንብ ቁጥር 1፤ የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 269/1955 እና የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ምደባና የደመወዝ ደረጃ ደንብ ቁጥር 2 (የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 419/1964) እንዲሁም የኮሚሽኑ መመሪያዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ካልተቃረኑ በስተቀር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 88 መሠረት በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

2. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ የይግባኝ ክርክሮች በዚህ አዋጅ መሠረት ይታያሉ።

3. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በቀድሞው ሕግ መሠረት ያገኘው መብት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ምክንያት አይቋረጥበትም።

91. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1996 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

8ኛ ዓመት ቁጥር 4
8th year No 4

ሐረር የካቲት 30 ቀን1996
HARAR 10th March,2004

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ 2.00 Unit Price Br | የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 P.O.BOX |


**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 35/96 ዓ.ም

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረት ሥራ ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ.......ገጽ 307


## አዋጅ ቁጥር 35/1996

## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት በመሰባሰብ ገንዘባቸውን እውቀታቸውንና ንብረታቸውን አቀናጅተው ያሉባቸውን ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ችግሮች በጋራ ለመፍታት የሚያስችላቸውን የህብረት ሥራ ማህበራት በአዲስ መልክ በማቋቋምና በማደራጀት በዚሁ ዙሪያ በመሰባሰብ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ከፍተኛ መሆኑን በማመን፤

እስካሁን በክልሉ ውስጥ የተደራጁና በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ድጋፍ ለጪነት ሲንቀሳቀሱ የነበሩት የህብረት ሥራ ማህበራት ለአባላቱም ሆነ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የሚጠበቅባቸውን ያህል አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ያለመቻላቸውንና በነበረው አሰራር ላቢያ የህብረት ሥራ ማህበራት ሊደራጁ የሚችሉባቸው ዘርፎች ተገድበው የቆዩ መሆኑን በመረዳት፤

በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት ለተቋቋሙና ወደፊትም በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቋቋሙ ማህበራት ድጋፍ በመስጠት የህብረት ሥራ ማህበራትን የሚያስፋፋና የሚያስተባብር ራሱን የቻለ መንግሥታዊ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ህገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ /2/ሀ/መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1- <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የህብረት ሥራ ማህበር ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2- <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

www.chilot.me

1- "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት ንዑስ አንቀጽ (1)፤ (9) ላይ የተመለከተው የሐረሪ ህዝብ ክልል ነው፡፡
2- "ምክር ቤት" ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው፡፡
3- "አዋጁ" ማለት የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ነው፡፡
4- "ማሕበር" ማለት በአዋጁ ቁጥር 147/1991 መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ ማንኛውም የህብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡ በተለይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል፡-
ሀ- የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት
ለ- የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበራት
ሐ- የኢንዱስትሪና የእደ ጥበብ የህብረት ሥራ ማህበራት
መ- የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት
ሠ- የማዕድን የህብረት ሥራ ማህበራት
ረ- የገንዘብ ቁጠባና ብድር የህብረት ሥራ ማህበራት፡፡
5- "የህብረት ሥራ ማህበር" ማለት ሰዎች በፍቃደኝነት ኢኮኖሚያዊ ችግርቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት መሠረታዊ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ማህበር ነው፡፡
6- "ጽ/ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመው የክልሉ መንግሥት የህብረት ሥራ ማህበር ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ነው፡፡
7- "ሥራ አስፈፃሚ" ማለት በክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተቋቋመው የክልሉ ከፍተኛ የህግ የአስፈፃ አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ጽ/ቤቱ መቋቋም አደረጃጀትና አላማ

3- **ስለ ጽ/ቤቱ መቋቋም**
1- የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የህብረት ሥራ ማህበር ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት የህግ ሰውነት ያለውና እራሱን የቻለ የክልሉ መንግስት አካል ሆና በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2- የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለሥራ አስፈፃሚ ይሆናል፡፡

4- **የጽ/ቤቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት**
1- በክልሉ መንግሥት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾም አንድ ኃላፊና ለስራው የሚያስፈልጉ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
2- የጽ/ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት ሐረር ከተማ ውስጥ ይሆናል፡፡

5- **የጽ/ቤቱ አላማዎች**
1- በክልሉ ቀደም ሲል በተለያዩ መ/ቤቶች አደራጅነት ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን የገበሬዎች የእደጥበብ ባለሙያዎች የገንዘብ ቁጠባና ብድር የመኖሪያ ቤቶች...ወዘተ የህብረት ሥራ ማህበራት በአዲስ መልክ የሚደራጁበትን መንገድ ማጥናት እነዚህንና ወደፊትም የሚቋቋሙትን ማህበራት በአለም አቀፍ የህብረት ሥራ መርሆዎች እና በአዋጁ መሠረት ማደራጀት የተደራጁትንም ማጠናከርና ማስፋፋት፤
2- በማህበራት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የንብረት እና የገንዘብ ብክነት መከላከል፤ አባላት በማህበራቸው ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው መርዳት፤
3- የህብረት ሥራ ጽንሰ ሃሳብን ለማስፋፋትና ለማዳበር ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከሚመለከታው አካላት ጋር በመተባበርም የአገር ውስጥና የውጭ አገር ስልጠናና የትምህርት ዕድሎች የሚገኙበትን ስልት መቀየስ፤
4- ማህበራት መገልገያና ማምረቻ መሳሪያዎችን፤ ጥሬ ዕቃዎችን የገበያና ብድር አገልግሎቶችንና የመሳሰሉትን በማግኘት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉበት ሁኔታ ማመቻቸት

## ክፍል ሶስት
## የጽ/ቤቱ እና የጽ/ቤት ኃላፊው ስልጣንና ተግባር

6- **የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር**
ጽ/ቤቱ በአዋጁ አግባብ ላለው ባለሥልጣን የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች የሚኖሩት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
1- ማህበራትን በሚመለከት በፌደራልም ሆነ በክልሉ የሚወጡ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
2- አለም አቀፍ የህብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ማህበራትን ያደራጃል፤ ይመዘግባል፤ የህጋዊ ሰውነት

www.chilot.me

ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ማህበር ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰርዛል፣

3- ማህበራቱ የፋይናንስ አቅማቸውን በማቀናጀት የማህበራት ባንኮች የሚቋቋሙበትን መንገድ አያጠና ያቀርባል:: ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

4- የማህበራት ማኔጅመንትና የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ አሠራር እንዲከተል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ሐባላት የቁጠባን ባህል እንዲያዳብሩና በማህበሮቻቸው ላይ የባለቤትነት ሥሜት እንዲያገለብቱ እገዛ ያደርጋል ለዚህም አስፈላጊውን የትምህርታዊ ስልጠና ፕሮግራም ዘዘጋጃል ይሰጣል፣

5- ስሥራው መቃናት የሚረዱ ተሞክሮዎችን ስመለዋወጥና ስመደጋገፍ አገባብ ካላቸው የክልልና የፌደራል መንግሥት አካላት ጋር ግንኙነትችን ያደርጋል፣

6- ማህበራትን ስማስፋፋትና ስማጠናከር የሚረዱ የጥናትና ምርምር ተግባራት ያካናውናል፣ የገበያ ጥናት በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀናብራል፣ ስሚመለከተውም አካል ያስተላልፋል:: እንዲሁም በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስማህበራት የሚሰጡ ማበረታቻዎችን ያጠናል፣

7- የማህበራትን ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦች አዘጋጅቶ በሥራ ላይ ያውላል፣

8- አገባብ ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ማህበራት ተገቢውን ድጋፍና እገዛ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፣

9- ማህበራት ያለምንም ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው መስራታቸውን ያረጋግጣል:: የማህበራት ገንዘብና ንብረት እንዳይባክን አስተማማኝ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋና ተገቢ ጥበቃ እንዲኖር ያደርጋል፣ የማህበራትን ሂሳብ ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፣በኦዲት ሪፖርት መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣ ወይም መወሰዱን ይከታተላል:: የማህበራትን የባከነ ገንዘብ እና ንብረት ስማስመለስ የሚያደርጉትን ጥረት ያግዛል፣

10- ህብረተሠቡ ስለ ማህበራት ጽንሰ ሐሳብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ስማድረግ በመገናኛ ብዙሃንና ሌሎችም ዘዴዎች የትምህርትና የቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል፣

11- በማህበራት መካከል የሚከሰቱ አስመግባባትን በሚመለከት በአዋጁ መሠረት የገልገል ተግባር ያካሂዳል::

ማህበራት የሚያቀርቧቸውን የመዋሃድ የመከፋፈልና የመፍረስ ጥያቄዎችን ተቀብሎ ይወስናል፣

12- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውሎችን ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ወይም ሊከሰስ ይችላል፣

13- ዓላማውን ስማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

14- ስዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦችን ያዘጋጃል ሲፀድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል::

7- <u>የጽ/ቤት ኃላፊው ስልጣንና ተግባር</u>

የጽ/ቤቱ ኃላፊ

1- የጽ/ቤቱን ሥራዎች ይመራል ያስተዳድራል

2- የጽ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል

3- በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት የጽ/ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል::

4- የጽ/ቤቱን በጀት እና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለክልል ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል::

5- ስጽ/ቤቱ በተፈቀደ በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል::

6- ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጽ/ቤቱን ይወክላል::

7- ጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ስክልል ሥራ አስፈጻሚ አዘጋጅቶ ያቀርባል::

8- ስጽ/ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ስሌሎች የጽ/ቤት ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

8- <u>ስለ በጀት እና የሂሳብ መዛግብት</u>

1- የጽ/ቤቱ የገንዘብ ምንጭ መንግሥትና ሌሎች ይሆናሉ::

2- የጽ/ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ሰነዶች በመንግስት ኦዲተሮች ይመረምራሉ፣

9- <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1- ቀደም ሲል በህብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 138/1970፣ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 85/1986 እና በክልሉ አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/88 መሠረት ማህበራትን ሲያደራጁ

www.chilot.me

የነበሩ የከብሉ መ/ቤቶች መብትና ግዴታዎች የህብረት ሥራ ማህበራትን በተመለከተ በዚህ አዋጅ ለጽ/ቤቱ ተላልፏል።

2- ስለሆነም ማህበራትን በማደራጀትና በማስተባበር ይሰሩ የነበሩ የተለያዩ የከብሉ መስሪያ ቤቶች ማህበራትን የሚመለከቱ ማናቸውንም ሰነዶችና መረጃዎች ለጽ/ቤቱ ያስተላልፋሉ።

10- <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማናቸውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል የዚህ አዋጅ እና በአዋጁ የተቀመጡት ድንጋጌዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

11- <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም

12- <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

ለዚህ አዋጅ አፈፃጸም የሚረዱ ደንቦችን የከልሉ ሥራ አስፈፃሚ ሊያወጣ ይችላል።

13- <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ጽ/ቤቱ ይህን አዋጅ እና ደንቡን በሥራ ላይ ለማዋል የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡

14- <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር የካቲት 30/1996 ዓ.ም

ፋአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

8ኛ ዓመት ቁጥር 3
8th Year NO 3

ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1996
HARAR 11th March,2004

የአንዱ ዋጋ
Unit price 1.00

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

ፖስታ ሳጥን ቁጥር
p.o.Box 272

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 36/1996 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ-------------------------------------------------------------------ገጽ 312

## አዋጅ ቁጥር36/1996

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ።

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ:

በክልሉ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ /2//ሀ/መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 36/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ማሻሻያ፤

የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1 የማቋቋሚያ አዋጁ ምዕራፍ አንድ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5) ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (6) ተጨምሯል።

«6 «ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ» ማለት በክልሉ መንግስት ሕገ-መንግስት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።»

2. ከማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 25 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተጨምሯል።

"26 ደንብ የማውጣት ሥልጣን
የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊውን ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።››

3. የማቋቋሚያ አዋጅ አንቅጽ 26 እና 27 እንደቅደም ተከተላቸው አንቅጽ 27 እና 28 ሆነዋል።

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከመጋቢት1 ቀን 1996 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት1 ቀን 1996ዓ/ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| ፰ኛ ዓመት ቁጥር 6<br>8th Year No 6 | | ሐረር መጋቢት 1ቀን 1996<br>HARAR 11th March, 2004 |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ<br>Unit Price 2.00 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O.Box 272 |

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 37/1996ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና
የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ........................................ገፅ 312

## አዋጅ ቁጥር 37/1996 የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ።

በዓለማችን ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ እድሜውን በማስፋት ምንም ሳይገድበው በተለይም በታዳጊ ሀገሮች በከፍተኛ ሁኔታ በመሠራጨት የጤና ችግር ብቻ መሆኑ ቀርቶ የልማት ችግር እየሆነ በመምጣቱ አምራች ዜጎችን የመኖር ህልውና በመፈታተን በማሳሰቡችም ሆነ በማኅበራዊና ስነልቦናዊ ቀውስ እያስተከለ በመገኘቱ፤

በአሁኑ ወቅት የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ በሽታ በአህጉራችን ከመቼውም ጊዜ በባሰ ሁኔታ ከዕለት ወደ ዕለት እያደረሰ ያለው ጉዳት እየተባባሰ በመምጣት በአገራችንም ሆነ በክልላችን ሁለንተናዊ ጉዳት ላይ እያንዣበበ ያለው አደጋ እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ ጥናቶች በመረጋገጡ የበሽታውን ሥርጭት ከወዲሁ መከላከልና መቆጣጠር ወቅታዊና የማይታለፍ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ፤

በክልላችን እስከ አሁን ድረስ በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መሠረት ያደረገና ያሳተፈ ከክልል እስከ ቀበሌ መዋቅር በመዘርጋት የመከላከሉን ሥራ ለመከወን ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም እነዚህ ጥረቶች በሀገር አቀፍ የኤድስ ፖሊሲ መሠረት ሁሉንም የብዙ ዘርፎችን ጥረት አቀናጅቶ ለመምራትና ለማስተባበር የሚያስችል ህጋዊ መሠረት ባለው መልኩ መዋቅሩ ካለመደራጀታቸውም በላይ ችግሩ የተወሳሰበና ባለብዙ ፈርጅ በመሆኑ እንደሚፈታ በመታመኑ፤

የብሔራዊውን የኤድስ ፖሊሲ ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ዋና ተግባሩ ወረርሽኙን መከላከል ሆኖ ኅብረተሰቡን መሠረት ያደረገና ያሳተፈ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ መከላከያ ፕሮግራም በመዘርጋት የብዙ ዘርፎችን ጥረት በማስተባበርና አቀናጅቶ በመምራት ተግባራዊነቱን የሚከታተል ህጋዊ የሆነ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ/2/ /ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ 'የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤትና የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 37/1996' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. 'ክልል' ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ ላይ የተመለከተው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ነው።
2. 'የሥራ አስፈጻሚ' ማለት ክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተቋቋመው የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚነት አካል ነው።

www.chilot.me

2. "የሥራ አስፈጻሚ" ማለት ከልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተቋቋመው የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚነት አካል ነው፡፡
3. "ምክር ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመው የክልሉ መንግሥት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ነው፡፡
4. "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት የተቋቋመው የምክር ቤቱ የሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡
5. "ሴክሬታሪያት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት የተቋቋመው የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ነው፡፡
6. "መከላከል" ማለት የበሽታውን መንስኤ ተህዋስ የሆነው ኤች.አይ.ቪ ወደ ጤነኛው የኅብረተሰብ ክፍል እንዳይተላለፍ ማድረግ ነው፡፡
7. "መቆጣጠር" ማለት የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ሥርጭት የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚወሰድ እርምጃ ነው፡፡

## 3. መቋቋም

የክልሉ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፡፡

## 4. የም/ቤቱ አጠቃላይ ዓላማ

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በክልሉ የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ ሥርጭትን ለመግታት፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
2. በክልሉ ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴን በተቀናጀ መልክ በማጎልበት ኅብረተሰቡ እራሱን ከወረርሽኙ በመጠበቅ የአሁኑም ሆነ ተከታዩ ትውልድ በኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ እንዳይጠቃ በማድረግ ለቀጣይ ዕድገት ጉዞ አስተማማኝ መሠረት መጣል፣
3. በ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ ሳቢያ እየደረሰ ያለው ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ መንቀሳቀስ፣
4. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ጠቅላላውን ኅብረተሰብ የሚያሳትፍ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ መርሃ-ግብር መዘርጋት፡፡

## 5. መርሆና ዓላማ

የምክር ቤቱ ጉባኤ ዓርማ «በቅንጅትና በቁርጠኝነት ኤች.አይ. /ኤድስ/ እንግታው ነገ ሳንል ዛሬ» የሚል መሪ ቃል የሰፈረበት ሆኖ ዓርማው መደቡ ቢጫ ሆኖ ዙሪያው በክልሉ ሰንደቅ ዓላማ የተከበበ ሊሆን መሐሉ ላይ ሁለት የተጣመሩ እጆች፣ ከፍ ብሎ መደቡ አረንጓዴ የሆነ እጅ ለእጅ በተያያዙ ሰዎች የተሞላ የክልሉ ካርታ፣ ካርታው መሐል ከታች ቀይ ሪባን ከላይ የብርሃን መቅረዝ የሚታይበት ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ ሁለቱ እጆች የክልሉን የኤድስ መከላከያ ምክር ቤት ይወክላሉ፣

ለ/ በክልሉ ካርታ ውስጥ ያለው የሕዝብ ምስል በምክር ቤቱ መሪነት ወረርሽኙን ለመከላከል ኅብረተሰቡ በቅንጅት መንቀሳቀስ እንዳለበት ያሳስባል፡፡

ሐ/ ቀዩ ሪባን በበሽታው የተያዙትንና የሞቱትን ለማስታወስ እንዲሁም ወላጅ አልባ ለሆኑት ሕፃናት እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ያሳስባል፡፡

መ/ ከቀዩ ሪባን በላይ የሚታየው የብርሃን መቅረዝ ኅ/ሰቡን ስለ ኤድስ በቂ ትምህርት እንዲያገኝ መደረግ እንደሚኖርበት ያመለክታል፡፡

## 6. መደበኛ አድራሻ

የምክር ቤቱ መደበኛ አድራሻ ሐረር ከተማ ይሆናል፡፡

## 7. ዝርዝር ዓላማዎች

1. የኤድስ በሽታን ለመከላከል አግባብ ያላቸው አካላት በሙሉ ለችግሩ ይበልጥ ትኩረትና ቅድሚያ ሰጥተው የኅብረተሰቡን ግንዛቤ፣ ተሳትፎና ድጋፍ ለማጎልበት በሙሉ ኃይላቸው እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
2. ለኤድስ የሚያጋልጥ የተሟላ ግንዛቤ እና ጤናማ ባህሪ እንዲጎለብት ኅብረተሰቡን መርዳት፣
3. ሴቶች፣ ወጣቶች ሌሎች ለበሽታው ይበልጥ የተጋለጡ የኅብረተሰቡ ክፍሎች እራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
4. የአገሪቷን የኤድስ ፖሊሲ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች መመሪያዎችና ስትራቴጂዎች በክልሉ ውስጥ በተቀናጀ መልክ እንዲተገበሩ ድጋፍ መስጠት፣
5. የአገሪቷ የኤድስ ፖሊሲ ከአጠቃላይ የጤና ፖሊሲ ጋር ተቀናጅቶ በክልሉ ተግባር ላይ የሚውልበትን ስልት መቀየስ፣
6. በኤድስ የተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች የጤና እንክብካቤ፣ የሥነ-ልቦና ምክርና እንደ ሁኔታው የማቴሪያል ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
7. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ የክልሉን ነዋሪ ህዝብ በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆችና ቤተሰቦቻቸው ሰብዓዊ መብት እንዲከበር ማድረግና ይኸውም በሌሎች መጠበቁን ማረጋገጥ፣
8. በኤድስ መከላከል ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሥልጠና እና ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፣
9. በተጠናከረና በተቀናጀ መልኩ ለችግሩ መፍትሄ የሚሆን ከአገር ውስጥና ከውጪ እርዳታ እንዲውል አመራር መስጠት፣ መከታተል፣
10. አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ እና እንዲጠናከር ድጋፍ ማድረግ፣
11. በየጊዜው የበሽታውን ሥርጭት ለመከታተል ለመገምገምና የወደፊት ተጨባጭ ዕቅድና ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት፣

# ክፍል ሁለት

# የክልሉ የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት አደረጃጀት፣ አወቃቀርና የሥራ አመራር

## 8. የምክር ቤቱ አቋም ምክር ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

1. የኤድስ መከላከያ ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ
2. የሥራ አመራር ቦርድ
3. የሴክሬታሪያት ጽሀፈት ቤት
4. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ
5. የቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ እና

www.chilot.me

6. እንደ አስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ

### 9. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት

1. ጠቅላላ ጉባኤው የምክር ቤቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡
2. ተጠሪነቱ ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

   ሀ/ የአገሪቱ የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ፖሊሲ እቅዶች ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍ ይሰጣል፤

   ለ/ በቦርዱ የሚቀርብለትን አመታዊ የሥራ ዕቅድ በጀት መርምሮ ያፀድቃል

   ሐ/ ለቦርዱ አስፈላጊውን አጠቃላይ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፤

   መ/ በቦርዱ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን ልዩ ልዩ ረቂቅ መመሪያዎችንና የማስፈጸሚያ ሥልቶች እየተመረመረ ያፀድቃል፤

   ሠ/ የሴክሬታሪያቱን የሥራ እንቅስቃሴ በቅርበት ይከታተላል፤ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርቱን ያዳምጣል፤ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

   ረ/ የገቢ ምንጮች የሚገኙበትን መንገድ ይቀይሳል ለአፈጻጸሙ ቦርዱና ሴክሬታሪያቱ አስፈላጊውን ድጋፍና መመሪያ እንዲሆንጁ ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፤

   ሰ/ ዓላማውን ሊያሳኩ የሚችሉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባኤው ከተግባርና ኃላፊነቱ ከፊሉን ለምክር ቤቱ ሥራ አመራር ቦርድ እንዲያከናውንለት ሊወክል ይችላል፡፡

### 10. ስለምክር ቤቱ ጠቅላላ አመራር ስብሰባና አሠራር ሥነ-ሥርዓት

1. የክልሉ ፕሬዚዳንት የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ በመሆን ይሰራል፤
2. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በየ6 /ስድስት/ ወሩ የሚካሄድ ሆኖ አስቸኳይ ጉዳይ ካጋጠመ ልዩ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል፤
3. የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
4. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ድምጽ እኩል የተከፈለ እንደሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤
5. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጠቅላላ ጉባኤው የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት የሚመለከቱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 11. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል ይመራል፤
2. የምክር ቤቱን ተልዕኮዎችና ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
3. የሥራ አመራር ቦርዱን እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል መመሪያዎችን ይሰጣል፤
4. ሴክሬታሪያቱን ያደራጃል፤ ኃላፊነቱን በክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት ያስፈጽማል፤
5. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለምክር ቤቱ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል፤
6. የምክር ቤቱ አባላትና የበጎ ፈቃድ ተሳታፊዎች እንዲበራከቱ ያበረታታል፤
7. በኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ መከላከል ዙሪያ አመርቂ ተግባራት ላከናወኑ ተቋማትና ግለሰቦች በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፤
8. በኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ መከላከል ዙሪያ በሚደረጉ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፍ ሲጋበዝ ይገኛል ወይም ሌሎች እንዲገኙ ይወክላል፤
9. በምክር ቤቱ ጥሪት የተገኙት የገቢ ምንጮች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
10. የምክር ቤቱ የሂሳብ መዛግብት አግባብ ባለው አካል እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡

### 12. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አባል ለመሆን ስለሚያበቁ ሁኔታዎች

1. በተዋረድም ሆነ በግል ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልተው የተገኙ ሁሉ በዚህ አዋጅ መሠረት የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

   ሀ/ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ/ን በክልሉ የመከላከሉ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶችና ኃይማኖታዊ ተቋማትን የሚወክሉ ኃላፊዎች፤

   ለ/ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ሰብዓዊ መብታቸውን በማስከበር ሌሎች ቫይረሱ የሌለባቸው ወገኖች እንዳይያዙ አስፈላጊውን የመከላከል ሥራ ለመሥራት የተደራጁ እና የእንቅስቃሴያቸውም አመርቂነት በምክር ቤቱ የሥራ አመራር ቦርድና ሴክሬታሪያቱ እየታየ የተመሰከረላቸው ማኅበራት መሪዎች፤

   ሐ/ በክልሉ ውስጥ በግላቸው ከፍተኛ የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴ በማድረግ ምስጉን አስተዋጽኦ ያላቸውና በተለይም ኤድስ የሚያደርሰውን አስከፊ የማኅበራዊ የኢኮኖሚያዊና የጤና ችግር በሚገባ በማመን በዚህ ዘርፍ ግዴታዎችን ለመወጣት ዝግጁ የሆኑ ታዋቂ ግለሰቦች፤

   መ/ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውና ትርጉም ያለው የማኅበረሰብ ተኮር ለማስከበር የተቋቋሙ የመያዣ የያዙና የቀድሞ መሠረት ያላቸው ሕዝባዊያንና የልማት ማኅበራት መሪዎች፡፡

2. ማንኛውም የአባልነት ጥያቄ በሴክሬታሪያቱ በኩል ከቀረበ በኋላ በሥራ አመራር የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 13. የአባልነት መብቶች

ማንኛውም አባል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ላይ የመገኘትና ሀሳብ የመስጠት፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ከተጠቀሰው የኃላፊነት እርከን ውጪ ባሉት የም/ቤቱ አመራር አካላት የመመረጥና የማገልገል፤
3. በምርጫ የሚለየው የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አመራር አካላትን የመምረጥ፤

### 14. የአባላት ግዴታዎች

ማንኛውም አባል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡

1. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ በሚያካሂዳቸው ስብሰባዎች ላይ የመገኘት፤

www.chilot.me

2. ሙያዊ ወይም ቁሳዊ እገዛ እንዲያደርግ በተጠየቀ ጊዜ የማበርከት፤
3. የምክር ቤቱ ዓላማዎች የሚፃረር ድርጊት ያለመፈጸም፤
4. በአባልነቱ ምክንያት ያወቃቸውን ምስጢሮች ሳይፈቀድለት ለሌላው ወገን አለመግለጽ፤
5. ምክር ቤቱ በመደበው ቦታ በቅንነት የማገልገል፤
6. በሚወክለው መሥሪያ ቤት፣ ድርጅት ወይም ማኅበር ውስጥ የሚካሄደውን ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር እንቅስቃሴ በቅርብ የመከታተል።

## 15. ከአባልነት ስለመሰናበት

በዚህ አዋጅ መሠረት በፈቃደኝነት የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አባል ሆኖ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው የአንድ ወር የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በቅድሚያ በመስጠት በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከአባልነቱ የመሰናበት መብት ይኖረዋል።

## 16. ከአባልነት ስለመሰረዝ

1. ማንኛውም የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አባል ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ከአባልነት ሊሰረዝ ይችላል።

ሀ/ የምክር ቤቱን ዓላማዎችና መርሆዎች የጣሰ እንደሆነ፤

ለ/ በአባልነቱ ምክንያት የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ተጠይቆ ግልጽ በሆነ መንገድ ተደጋጋሚ ቸልተኝነት የታየበት እንደሆነ፤

ሐ/ የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ በሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ከአባልነቱ እንዲሰረዝ የወሰነ እንደሆነ፤

አባልነቱ ከተቋረጠ ወይም ከማኅበሩ የሥራ ባህሪ የመነጨና የተሰረዘውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት በተቀመጡ ምክንያት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ አግባብ ባለው የሥራ ኃላፊ አማካኝነት በተተካው ላይ አስፈላጊው የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ ለሚወክለው አካል ሪፖርት ማድረግ ይቻላል።

## ክፍል አራት
## ስለ ሥራ አመራር ቦርድ

## 17. ስለ ሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም

1. አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ያካተተ የምክር ቤቱ የሥራ አመራር ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤
2. የቦርዱ አባላት በምክር ቤቱ ይመረጣሉ፤
3. ቦርዱ ከአባላቱ መካከል በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሰብሳቢ ሲኖረው የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ በፀሐፊነት ያገለግላል፤
4. የሥራ አመራር ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ እንደ አስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል፤
5. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሴክሬታሪያቱ በሚገኝበት ስፍራ ይሆናል።

## 18. ስለ ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች በሽታውን በመከላከልና በመቆጣጠሩ ሥራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
2. በሴክሬታሪያቱ ተዘጋጅቶ የሚቀርቡለትን የምክር ቤቱን አመታዊ የሥራ ዕቅድና የማስፈጸሚያ በጀት ረቂቅ መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. በሥራው መታየት የሚያገዙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ያደራጃል ሥራዎቻቸውንም በቅርብ ይከታተላል ይገመግማል፤
4. በሥልጣኑ ሥር የተቋቋሙትን ኮሚቴዎች ሰብሳቢና ፀሐፊ ይሰይማል፤
5. በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ የሚተላለፉትን ውሳኔዎችና የሚሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. ስለ አከናወናቸው ተግባራት ለጠቅላላ ጉባኤው ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤
7. የሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤት የሚያቀርባቸውን ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ይገመግማል፤

## 19. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ/18/ የተደነገጉት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. የቦርዱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል ይመራል፤
2. የቦርዱን ተልእኮዎችና ሥራዎችን በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል፤
3. ከሴክሬታሪያቱ የሚቀርቡ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እንዲገመገሙ ያደርጋል፤ ያፀድቃል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
4. ከዚህ በተጨማሪ ከጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

## ክፍል አምስት
## ስለ ምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት መቋቋም
## ተጠሪነትና ኃላፊነት

## 20. ስለምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት

1. የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች የሚያከናውን የሴክሬታሪያት ጽህፈት ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፤
2. ሴክሬታሪያቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 የተዘረዘሩት ተግባራትና ኃላፊነቶች በሚኖሩበት በአንድ የበላይ ኃላፊ የሚመራ ሲሆን በየደረጃው ጽህፈት ቤትና በተዋረድ እስከታች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል።
3. የሴክሬታሪያቱ ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል።
4. የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ የምክር ቤቱም ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል።

## 21. የሴክሬታሪያቱ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 እና 18 ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤና ለሥራ አመራር ቦርዱ የተሰጣቸው አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

1. በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችና የሥራ ፕሮግራሞች ላይ በመመስረት የኤድስ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ የሚደረጉበትን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
2. ምክር ቤቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥልት ይቀይሳል።
3. የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ በሽታን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ታዋቂ ግለሰቦችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል፤

www.chilot.me

በመካከላቸው የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

4. ኅብረተሰቡ የቫይረሱን መተላለፊያ መንገድ አውቆ እንዲከላከል ተስማሚ የትምህርት መረጃ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት ትምህርት ለሚሰጡ አካላት አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

5. በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስን/ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ አገር አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፤

6. በክልሉ የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ን ገጽታ በሚመለከት መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤ እንደአስፈላጊነቱም ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስተላልፋል፤

7. ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ በመከላከልና በመቆጣጠር ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የሙያ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲሰጥ ያስተባብራል፤

8. በሥልጣኑ ሥር የተቋቋሙትን ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ተግባር በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤

9. የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድና በጀት ረቂቅን አዘጋጅቶ በሥራ አመራር ቦርድ አማካኝነት ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባር ላይ ያውላል፤

10. የምክር ቤቱን ጠቅላላ ጉባኤና የቦርዱን ውሳኔዎች ለክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ያስተላልፋል በወቅቱ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

11. ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፤

12. በሕጉ የተገኘውን ገንዘብና ከመንግሥት የሚመደበውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ያውላል፤

13. በክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች ህግና ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

14. ምክር ቤቱን ወክሎ ይከሰሳል፤ የንብረት ባለቤትም ይሆናል፤

15. የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ለቦርዱና ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

16. በምክር ቤቱ እና በሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ስድስት

## ስለ ምክር ቤት ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

### 22. ስለ ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ መቋቋም

1. ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት ገቢና ወጪውን የሚከታተልና የሚቆጣጠር የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፤

2. የኮሚቴው ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤

3. የኮሚቴው አባላት በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይሰየማሉ።

### 23. ስለ ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. የሴክሬታሪያቱን ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ ይመረምራል፤

2. የሴክሬታሪያቱን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸውንና ለተፈቀደው አገልግሎት ብቻ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

3. በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ መመሪያ ሊሰጠው ድንገተኛ የሂሳብ ምርመራ ያደርጋል፤

4. የራሱን የውስጥ አሠራር መመሪያ በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ያቀርባል ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤

5. ከጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ሰባት

## በቀበሌ ደረጃ የፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴዎች አደረጃጀትና የሥራ አመራር

### 24. ስለ ቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ መቋቋም

1. ተጠሪነቱ ለሴክሬታሪያቱ የሆነ አምስት አባላት ያሉት ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት በቀበሌ ደረጃ ተቋቁሟል፤

2. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል፤ ሆኖም ድንገኛ አይታገድም፤

3. የቀበሌው ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በአንቀጽ፡ ቁጥር24 በንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተጠቀሰው ሆኖ ኮሚቴው የሚከተሉትን ቅንጅታዊ አባላትና ተዋጽኦ በክፍል ያካተተ ይሆናል።

ሀ/ የቀበሌው ሊቀመንበር /ሰብሳቢ/

ለ/ የሴቶች ተወካይ /አባል/

ሐ/ የወጣቶች ተወካይ /አባል/

መ/የኃይማኖት ድርጅቶች ተወካይ /አባል/

ሠ/ ታዋቂ ግለሰቦች /አባል/

ረ/ የቀበሌው የጤና ኮሚቴ ሰብሳቢ /አባል/

ሰ/ ከቫይረሱ ጋር አብሮ የሚኖር ግለሰብ /አባል/

ሸ/ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ግለሰቦች /አባል/

ቀ/ በቀበሌው ሥራ አስፈጻሚ የሚሰየም /ፀሐፊ/

### 25. የቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የቀበሌ ፀረ-ኤድስ አስተባባሪ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. በቀበሌው ውስጥ በኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ መከላከል ዙሪያ ለሚሰሩ ሥራዎች እቅዶችን ያወጣል ይተገብራል፤

2. በቀበሌው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ዙሪያ የሚደረገውን ሁለገብ እንቅስቃሴ ያስተባብራል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

3. የቀበሌው ነዋሪ ኅብረተሰብ ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ በሚያስከትለው ጉዳት ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ በተለያዩ ስብሰባዎች ከሴክሬታሪያቱ ጋር በመነጋገር ትምህርት ይሰጣል፤

4. በበሽታው ለተያዙ ግለሰቦች አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤

5. የቀበሌውን የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ ገጽታ በሚመለከት መረጃዎች ያሰባስባል ያጠናክራል እንደ አስፈላጊነቱ ለሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፤

6. ማኅበረሰቡ ለተለያዩ አላማዎች የሚያቋቁማቸውን የእድር የማኅበርና የእቁብ ተቋማት ወዘተ... በመጠቀም ኅብረተሰቡ በኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ ላይ ያለውን ግንዛቤ እንዲያሳድግ ይንቀሳቀሳል፤

7. ለሴክሬታሪያቱ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

8. ከሥራው ባህሪያት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

www.chilot.me

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 26. የሴክሬታሪያቱ የገቢ ምንጭ

የሴክሬታሪያቱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. ከክልሉ መንግሥት የሚመደብ በጀት፤
2. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ለጋሽ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች የሚገኝ የቴክኒክና የቁሳቁስ ድጋፍ፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር የተደነገገውን ተግባራዊ ለማድረግ ምክር ቤቱ ራሱን የቻለ የገቢ አሰባሳቢ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

### 27. ስለ ሴክሬታሪያቱ የበጀት ዓመት

የምክር ቤቱ የበጀት አመት የክልሉ መንግሥት የሚሰራበት የበጀት አመት ይሆናል፡፡

### 28. ስለ በጀት አስተዳደርና ሂሳብ አያያዝ

1. ሴክሬታሪያቱ የራሱን ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሳብ በሴክሬታሪያቱ ስም ይከፍታል፤
2. ሴክሬታሪያቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ ሠነዶችና መዛግብት የመያዝ ግዴታ አለበት፤

### 29. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

የኤድስ መከላከያና መቆጣጠር ተግባራትን አስመልክቶ እስከ አሁን ድረስ በክልሉ ውስጥ የሚሰራበት ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 30. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ምክር ቤቱ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 31. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሥራ አመራር ቦርዱ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦች አዘጋጅቶ ለክልሉ መንግሥት የሥራ አስፈጻሚ በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡

### 32. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት እለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መንግሥት

ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

የሐረሬ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| 8ኛ ዓመት ቁጥር 7<br>8th Year No 7 | ሐረር - መጋቢት 1 ቀን 1996<br>HARAR -10th March ,2004 |
|---|---|

| ያንዱ ዋጋ ብር<br>Unit price Br 2.00 | በሐረሬ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O Box 272 |
|---|---|---|

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 38_1996 ዓ.ም
የሐረሬ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ -------------------- ገጽ319

## አዋጅ ቁጥር 38/1996
## የሐረሬ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሎም በክልሉ ህገ መንግሥት ታማኝና በህገ መንግሥቱ መሰረት ለሚወጡ ሕጎች ተገዥ የሆነ ለሙያው በቂ የሆነ ሥልጠና የተሰጠውና ብቃት ያለው ለህዝብ አገልጋይና ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያከብር እንዲሁም የህዝብን ሠላምና ደህንነት የሚያረጋግጥ የተጠናከረ ሲቪል የፖሊስ ተቋም በማቋቋም ስልጣንና ተግባርን በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በሐረሬ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (2) (ረ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## 1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የሐረሬ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/1996 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

ሀ. " ክልል " ማለት የሐረሬ ሕዝብ ክልል ማለት ነዉ፡፡

ለ. " ፖሊስ" ማለት መሰረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ስልጠና ተሰጥቶት በኮሚሽኑ ተቀጥሮ የሚሰራ የሐረሬ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን አባል ነው፡፡

ሐ. "ሥራ አስፈፃሚ "ማለት በክልሉ ሕገ- መንግስት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ስልጣን የተሰጠው አካል ነው ፡፡

መ. "ኮሚሽን " ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሰረት የተቋቋመው የሐረሬ ሕዝብ ብሔራዊ ካልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ነው ፡፡

## 3. መቋቋም

1. የሐረሬ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የክልሉ መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ኮሚሽኑ በሕግና በሙያ የሚኖረው ነፃነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡

## 4. የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት ሐረር ከተማ ይሆናል፡፡

## 5. የኮሚሽኑ ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ የሐገሪቱንና የክልሉን ሕገ መንግስት እንዲሁም ሌሎችን ሕጎች በማስከበር እና በማክበር የሕዝብን ተሳትፎ መሠረት በማድረግ ወንጀልን በመከላከል የህዝብን ሠላማዊ ኑሮና ፀጥታ ማስጠበቅ ነው፡፡

## 6. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

1. ማንኛውንም ወንጀል ይከላከላል፤
2. በክልሉ ፍርድ ቤት ስልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን ይመረምራል፤
3. በህግ የዳኝነት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይንም ውሳኔ ይፈፅማል፤
4. የወንጀል ምርመራን በተመለከተ ከክልሉ ዐቃቤ ህግ የሚሰጠውን መመሪያ ይፈፅማል፤
5. ዋና ዋና የክልሉን ተቋሞች እንዲሁም የህዝቡን ህይወትና ንብረት ይጠብቃል፤
6. በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እርዳታ የመስጠትና የተጎዱ ሰዎች አፋጣኝ እርዳታ እንዲያገኙ በማድረግ ከሚመለከታቸው ጋር ይተባበራል፤

www.chilot.me

7. ለከፍተኛ የክልሉ መንግስት ባለስልጣናት እና ለውጭ አገር እንግዶች ጥበቃ ያደርጋል፣
8. ከወንጀል ነፃ የመሆን ማስረጃ ይሰጣል፣
9. የወንጀል መነሻ ምክንያቶችን በማጥናት የመከላከል ዘዴዎችን ይነድፋል፣
10. ከፌዴራልና ከሌሎች ክልሎች ግንኙነት በመፍጠር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣
11. ሙሉ የማያቋርጥ የንብረት ባለቤት የመሆን በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፣
12. በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ፖሊስ ማሰልጠኛዎችን ያቋቁማል፣
13. ለክልሉ ፖሊስ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ምልምሎ በማሰልጠን በአስፈላጊው ቦታ ይመድባል፣
14. የመንገድ ላይ ትራፊክ እንቅስቃሴና ደህንነት ይቆጣጠራል፣ የትራፊክ አደጋዎች ሲያጋጥሙ መንስኤያቸውን ይመረምራል፣
15. ለሥራው የሚያስፈልጉት ድጋፍ ሰጪ ሲቪል ሰራተኞችን በመንግስት ሰራተኞች ደንብና መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል
16. በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በውል ተለይተው በውክልና የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
17. የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ከለሙ ድርጅቶች ወይም ወኪሎች ጋር በትብብር ይሰራል፣
18. በማስረጃነት ወይም በኤግዚቢትነት የሚያዙ ንብረቶችን በአግባቡ ጠብቆ ይይዛል እንደአስፈላጊነቱ በህግ አግባብ ይመልሳል፣
19. ፣ ለምርመራ ሥራ የሚረዱ ማስረጃዎችን ለማግኘትና ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን ለመስጠት የቴክኒክ ምርመራ ያደርጋል፣
20. ከህዝብ ለሚጠየቅ እርዳታ አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፣

## 7. የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ፡-

1. በክልሉ መንግስት የሚሾም አንድ ኮሚሽነር
2. ኮሚሽነሩንና ረዳት ኮሚሽነሮችን ያቀፈ የሥራ አመራር ጉባኤ እና
3. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች ፖሊሶችና የሲቪል ሰራተኞች ይኖሩታል።
4. የኮሚሽኑ አደረጃጀትና አወቃቀር የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

## 8. የኮሚሽኑ ሥራ አመራር ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

የኮሚሽኑ ሥራ አመራር ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

1. የኮሚሽኑን አደረጃጀት አወቃቀርና አሰራር የሰው ኃይል ግንባታ በሚመለከት የሚደረጉ ጥናቶችን የአቅም ግንባታ መርሀ ግብር አተገባበሮችን ረቂቅ በመመርመር እንዲፀድቅ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል።
2. የከፍተኛ ስልጠና ዕቅድ በማዘጋጀት አባሎች እንዲሰለጥኑ ያደርጋል ።
3. የኮሚሽኑን ዓመታዊ ዕቅድ ሪፖርትና የሥራ አፈፃፀም በመገምገም ከአስተያየት ጋር ለ ክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል።
4. ከፌደራልም ሆነ ከሌሎች ክልል ፖሊሶች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል
5. የኮሚሽኑን ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል፣ እንዲጸድቅለትም ለክልሉ መንግስት ያቀርባል ።
6. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም፡ -
   ሀ/ በኮሚሽኑ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ደንቦችን መርምሮ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ያቀርባል፣
   ለ/ በኮሚሽኑ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ መመሪያዎችን መርምሮ ያፀድቃል፣
7. በደንብና መመሪያ መሠረት ተጣርተው በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።
8. የክፍል እና ንዑስ ክፍል ኃላፊዎችን ምደባ በደንቡ መሠረት ይፈፅማል።
9. ከረዳት ኮሚሽነር በታች ያሉ ልዩ ልዩ የማዕረግ ተሿሚዎችን ሹመት በደንቡ መሠረት መርምሮ ያፀድቃል።

## 9. የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ሆኖ የኮሚሽኑን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር/1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡ -
   ሀ/ የኮሚሽኑን ረዳት ኮሚሽነሮች እንዲሾሙ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል።
   ለ/ ከረዳት ኮሚሽነሮች በታች ያሉ ልዩ ልዩ የማዕረግ ተሿሚዎችን ለይቶ ለኮሚሽነሮች የሥራ አመራር ጉባኤ ያቀርባል፣
   ሐ/ የክልሉን ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ ያስፈፅማል፣
   መ/ በክልሉ ፖሊስነት ከተቀጠሩት ውጪ ያሉትን ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ያስተዳድራል፣
   ሠ/ በክልሉ ፖሊስ አባላትም ሆነ በኮሚሽኑ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እንዲጣሩ በማድረግ ለኮሚሽነሮች ሥራ አመራር ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል ጉባኤው የሰጠውንም ውሳኔ ለአቤቱታ አቅራቢው ያስታውቃል፣
   ረ/ የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
   ሰ/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
   ሸ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል
3. የኮሚሽኑን የሥራ እንቅስቃሴ የማስተባበርና አመራር የመስጠት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣
4. ከፌደራል እና ከክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል የአቅም ግንባታ መንገዶችን ያፈላልጋል።
5. የኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለረዳት ኮሚሽነሮች ወይም ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።
6. የኮሚሽኑን አጭር የመካከለኛ የረጅም ጊዜ ዕቅድ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፣
7. ስለ ስራው አፈጻጸም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል ።

## 10. ረዳት ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር

1. ረዳት ኮሚሽነሮች ተጠሪነታቸው ለኮሚሽነሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል ፡ -

www.chilot.me

ሀ. በየሥራ ዘርፋቸው የሚመለከታቸውን ተግባሮች በማቀድ በማደራጀት በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳሉ፤

ለ/ በኮሚሽኑ መዋቅር መሰረት የሥራ ክፍፍሎች በማድረግ የኮሚሽኑን የስራ ዘርፎች ይከታተላሉ፤

ሐ/ በኮሚሽነሩ ሲወከሉ ተክተው ይሰራሉ፤

መ/ በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ፤

ሠ/ ዝርዝር ተግባራቸው በሚወጣው መዋቅር ይገለጻል፡፡

## 11. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል.

## 12. ስለ ሂሣብ መዛግብት

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፤
2. የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በኦዲት ቢሮ ወይንም ኦዲት ቢሮ በሚሰይመው ኦዲት ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ ክልሉ ፖሊስ አስተዳደር

## 13. ለፖሊስነት የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በክልሉ በፖሊስነት ለመመልመል የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል ፡፡
   ሀ. በፖሊስነት ለማገልገል ፍቃደኛ የሆነ፤
   ለ. ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት ብሎም ለክልሉ ሕገ መንግስት ታማኝ የሆነ፤
   ሐ. በክልሉ ፖሊስነት ለመመልመል የሚያስፈልገው የትምህርት ደረጃና አካላዊ ብቃት የሚያሟላ፤
   መ. በህብረተሰቡ ውስጥ በዲሲፕሊኑ ወይም በሥነምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤
   ሠ. ከዚህ በፊት በወንጀል ድርጊት ውስጥ ለመሣተፉ ሪከርድ የሌለበት፤
   ረ. ዕድሜው ከ18ዓመት ያላነሰ፤
   ሰ. የክልሉን የስራ ቋንቋ የሚችል
2. የፖሊስ ምልመላ በህዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የተመለመለ ሰው የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆነ እንደሆነ የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን መልቀቅ ይኖርበታል።

## 14. ቃለ መሐላ ስለመፈፀም

1. በክልል ፖሊስነት የተመለመለ የተጣለበትን ህዝባዊና ሙያዊ አደራ በታማኝነትና በታታሪነት ለመጠጣት ቃለ መሀላ ይፈፅማል፡፡
2. የቃለ መሀላ ይዘት በደንብ ይወሰናል፡፡

## 15. ለሲቪል የመንግሥት ሰራተኞች የፖሊስ ስልጣን ስለመስጠት፡፡

1. ልዩ ሙያ ለሚጠይቁ ጉዳዮች ለሲቪል የመንግሥት ሠራተኛ የፖሊስ ስልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚሰጠው የፖሊስ ስልጣን ለጉዳዩ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

## 16. የአገልግሎት ዘመን

1. የማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንቡ ይወሰናል፡፡
2. የማንኛውም የክልሉ ፖሊስ ግዴታ አገልግሎት በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣል፡፡

   ሀ/ በሞት
   ለ/ የስንብት ጥያቄ ቀርቦ በደንቡ መሰረት ተቀባይነት ሲያገኝ፡፡
   ሐ/ በሐኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ህመም ለሥራው ብቁ ሳይሆን ሲቀር፤
   መ/ በፍ/ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና ወንጀሉ ለሥራው ብቁ አያደርገውም ተብሎ በኮሚሽኑ ሲወሰን ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል ፡፡
   ሠ/ በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ይቋረጣል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤
   ረ/ በጡረታ ሲገለል ፡፡

## 17. መብት

1. ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል
   ሀ/ በመንግሥት በሚወጽት የደመወዝ እስኬል መሰረት ደ□ወዝ ያገኛል□

   ለ/ በኮሚሽኑ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ቀለብ ልዩ ልዩ አበሎች የደንብ ልብስና የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤
   ሐ/ በጡረታ ሕግ መሰረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፤
   መ/ ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣትላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት መስሪያ ቤቱ ጠበቃ ያቆምለታል ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፤
   ሠ/ በማንኛውም አጋጣሚ ኃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ ስህተት ሲያይ የመጠቆም በውይይት ችግሮችን የመፍታት መብት አለው አስፈላጊ ሲሆን የስልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤
   ረ/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደርስበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመስራት ችሎታውን ያጣ ፖሊስ አግባብ ባለው የጡረታ ህግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል፤

www.chilot.me

ሸ/ በኮሚሽኑ ውሳኔ ከሥራ የሚሰናበት አባል ይግባኝ በተመለከተ የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ በሚያቋቁመው አካል ይታያል ፣ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል::

2. በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ውጭ ያሉ መብቶችን በተመለከተ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጎች በፖሊስ አባላት ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ::

## 18. ግዴታ

ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ

1. በሕገ መንግሥት የተረጋገጡትን የሰበአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፍ በማክበር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት ሥራውን የማከናወን፣
2. ፖሊሳዊ ሥራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ እና ባጅ የማሳየት ግዴታ አለበት።

## 19. የጡረታ መውጫ ዕድሜ

ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል በጡረታ የሚገለልበት ዕድሜ ጣሪያ አግባብነት ባለው የጡረታ ሕግ መሰረት ለመንግስት ሰራተኞች የተወሰነው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ይሆናል ።

## 20. ወታደራዊ ማዕረግ ስለመቅረቱ

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የክልሉ ፖሊስ ወታደራዊ ማዕረግ አይኖረውም ይህን የሚተካ የፖሊስ የሆነ ማዕረግና ምልክት ይኖራል ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል ።
2. የክልሉ ፖሊስ አባል የሥራ መደብን የሚያመለክት የመለያ ደንብ ልብስ እንዲሁም ማንነቱን የሚገልጽ ስም ቁጥር ክፍሉንና ኃላፊነቱን የያዘ ባጅ ወይንም ምልክት ይኖረዋል ።

## 21. አሰራር

1. በክልሉ ፖሊስ መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር ዋና የተግባር አፈፃፀም አቅጣጫ ይሆናል።
2. በክልሉ ፖሊስ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ስልጣን በመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው።
3. ከሥራ እቅድ አመዳደብ እስከ አፈፃፀምና ግምገማ ድረስ የክልሉ ፖሊስ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በቡድንና በቅንጅት ይሠራሉ የቡድን አሠራሮች የጋራና የግል ኃላፊነትን ያስከትላሉ።
4. የፖሊስ አሰራር የህዝብ ተሳትፎን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

## 22. የተከለከለ ድርጊት

ማናቸውም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝና ድርጊት የተከለከለ ነው።

## 23. ስለ ክልሉ ፖሊስ አቤቱታ ሰሚ

1. በኮሚሽኑ ውስጥ የክልሉ ፖሊስ አቤቱታ ሰሚ አካል ይቋቋማል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 24. ኮሚሽኑ ከሌሎች ከክልልና ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

1. ኮሚሽኑ የክልሉን ፖሊስ ጉዳዩች በሚመለከት ከሌሎች ከክልልና ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል።
2. የክልሉ ወንጀል ትራፊክና ፀጥታን በሚመለከት ሪፖርትና ስታትስቲክስ ሲጠየቅ ለጥናት ለወል ጠቀሜታ እንዲውል ሲባል ለፌዴራል ፖሊስ ያስተላለፋል::
3. ለጋራ አላማ ሲባል በፌደራል ፖሊስ አስተባባሪነት በሚጠሩ ጉባኤዎች ላይ ኮሚሽኑ ይገኛል።
4. በጋራ ጉባኤያቸው የሚከተሉትን ተግባራት አብሮ ይሰራል፡-
   ሀ/ የጋራ አሰራር ደንብ በማውጣት፣
   ለ/ የወንጀል መከላከልና ምርመራ እንቅስቃሴዎችን ገምግሞ የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣
   ሐ/ የፖሊስ ስልጠናን በተመለከተ የጋራ አቅጣጫዎችን በመቀየስ።

## 25. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ህግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 26. ደንብና መመሪያን የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

## 27. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት እለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 1/1996 ዓ.ም
ፋስድ ሰብራሂም
የሐረሪ ህዝብ ብ/ ክ/ መንግስት ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ፰ኛ ዓመት ቁጥር 8<br>8th year No.8 | | ሐረር መጋቢት 1/1996<br>HARAR 11 th March 2004 |
| ያንዱ ዋጋ<br>Unit price Br 2.00 | በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.o.Box - 272 |


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 39/1996 ዓ.ም
የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ........................ገፅ 322

## አዋጅ ቁጥር 39/1996
## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ማረሚያ ቤቶች የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በመፈጸም ሂደት ታራሚዎችን የመጠበቅና የማረም ተግባራትን በማከናወን ወንጀልን በመከላከል ረገድ የበኩላቸውን ተገቢ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በመሆኑ

ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና ለክልሉ መንግስት ሕገ መንግስት ታማኝና በሕገ-መንግስቱ መሠረት ለሚወጡ ሕጎች ተገዥ የሆነ የክልል ማረሚያ ቤቶች ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ 26/2/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 39/1996›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. « ክልል » ማለት የሐረሪ ሕዝብ ክልል ነው።
2. « ኮሚሽን » ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ነው።
3. « ሥራ አስፈፃሚ » ማለት በክልሉ ሕገ መንግስት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።
4. « ማረሚያ ቤት » ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የሚላኩ ታራሚዎች የተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት የሚፈጽሙበት የሚታረሙበት፤ እንዲሁም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚላኩ ውሳኔ እስከሚያገኙ እንዲቆዩ የሚደረግበት የክልል ማረሚያ ተቋም ነው።
5. « ታራሚ» ማለት በሕግ ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የፍርድ ውሳኔ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በመፈጸም ላይ የሚገኝ የሕግ ታራሚ ሲሆን በማረሚያ ቤት በቀጠሮ እንዲቆይ የተወሰነበትንም ይጨምራል።
6. « የማረሚያ ጠባቂ » ማለት መሠረታዊ የሆነ የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በኮሚሽኑ ተቀጥሮ የሚሠራ የክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን አባል ነው።

### ክፍል ሁለት
### ስለ ኮሚሽኑ መቋቋም

### 3. መቋቋም

1. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ኮሚሽኑ በህግና በሙያ የሚኖረው ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈፃሚ ይሆናል።

### 4. የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት

1. የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት ሐረር ከተማ ይሆናል
2. ኮሚሽኑ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር የሚያከናውኑ አካላትን በክልሉ በማናቸውም ቦታ ማቋቋም ይችላል።

www.chilot.me

## 5 ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ ታራሚዎችን ተቀብሎ መጠበቅ ለታራሚዎች የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠት የአስተሳሰብና የስነ- ምግባር ለውጥ እንዲያመጡ እንዲሁም ሕግ አክባሪ ሰላማዊና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

## ፩. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት የሚላኩለትን ታራሚዎች በመቀበል ይጠብቃል፣ ያርማል እንዲሁም ከፍርድ ቤት የሚሰጡ ሌሎች ትእዛዞች ይፈጽማል፣
2. ታራሚዎችን ፍርድ ቤት ያቀርባል፣
3. የታራሚዎችን ጤንነት ይጠብቃል፣ በዚህ አዋጅ በሚወጣው ደንብ መሠረት ታራሚዎች ነጻ ህክምና ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል ለታራሚዎች አካላዊና አእምሮአዊ እንክብካቤና አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ያከናውናል፣ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ፣
4. ታራሚዎች ከተለቀቁ በኋላ ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚችሉና ለሕግ ተገዢ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የቀለም ትምህርት፣ የሙያ ስልጠና የማህበራዊና የምክር አገልግሎት ይሰጣል ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣
5. ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የማረሚያ ቤቱን የስነ- ሥርዓት መመሪያ በመጣስ ለሚፈጽሙት ጥፋት በዚህ አዋጅ በሚወጣው ደንብ መሠረት የሥነ-ስርዓት ቅጣቶችን ይወስናል ይፈጽማል፣
6. በክልል አቀፍ ደረጃ ታራሚዎችን በሚመለከት መረጃዎችን እና ስታትስቲኮችን ያሰባስባል ያጠናቅራል፣
7. ታራሚዎች በሚያሳዩት የባህሪይ ለውጥ በሕግ መሠረት
   ሀ. በአመክሮ፣
   ለ. በይቅርታ እንዲፈቱ ስልጣን ለተሰጠው አካል ሃሳብ ያቀርባል፣
8. ኮሚሽኑ ለስራ አስፈላጊ የሆኑ የማረሚያ ጥበቃ አባላት ይመለምላል፣ ይቀጥራል፣ ያሰለጥናል፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፣
9. የኮሚሽኑን ሠራተኞች የሞያ ብቃት ለማሳደግ በሐገር ውስጥና በውጭ ሀገር የስልጠና እድሎችን ያመቻቻል፣
10. የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል የማረሚያ ጥበቃ አባላትና ሠራተኞችን ሞያ ብቃትና አገልግሎት በሐገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፣
11. ውል ይዋዋላል በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

## 7. የኮሚሽኑ አቋም

1. ኮሚሽኑ
   ሀ. በክልሉ ምክር ቤት የሚሾም አንድ ኮሚሽነር፣
   ለ. ኮሚሽነሩንና ለኮሚሽነሩ ተጠሪ የሆኑትን ረዳት ኮሚሽነሮችን ያቀፈ የሥራ አመራር ጉባኤ እና
   ሐ. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች፣ የማረሚያ ጥበቃ አባላትና ሲቪል ሠራተኞች ይኖሩታል፣
2. የኮሚሽኑ አደረጃጀት ዝርዝርና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች በስራ አስፈጻሚ ይወሰናል።

## 8. የሥራ አመራር ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ጉባኤው

1. ለፌዴራልና ለክልል ሃላፊዎች የጋራ ጉባኤ በሚቀርቡ የታራሚዎችን አጠባበቅ አያያዝና የማረሚያ ቤቶችን አስተዳደር ለማሻሻል የሚረዱ ተመርምረው ከአስተያየት ጋር በሚቀርቡ ሀገር አቀፍ የፖሊሲ፣ የስትራተጂና የስታንደርዳይዜሽን ጥናቶች ላይ በመሳተፍ በክልሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል፣
2. የኮሚሽኑን አደረጃጀት አወቃቀርና አሠራር የሚመለከቱ ጥናቶችን ይመረምራል ሊወሰዱ በሚገባቸው እርምጃዎች ላይ ይወያያል፣ አስተያየት ይሰጣል፣
3. የኮሚሽኑን የስልጠና እቅድ ያዘጋጃል፣
4. በተዘጋጀው የኮሚሽኑ የሥራ እቅድና ረቂቅ በጀት ላይ ተወያይቶ በክልሉ መንግስት እንዲጸድቅለትም በኮሚሽነሩ በኩል ለሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፣
5. የኮሚሽኑን ዓመታዊ እቅድ አዲትና ሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣ ከአስተያየት ጋር ለሥራ አስፈጻሚ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በኮሚሽነሩ በኩል ለምክር ቤት እንዲቀርብ ያደርጋል፣
6. ኮሚሽኑ ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽንና ከሌሎች ክልል ማረሚያ ቤቶች ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል።

## 9. የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

1. የኮሚሽነሩ ተጠሪነት ለክልሉ ፕሬዝዳንት ሆኖ የኮሚሽኑን ሥራ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ ፣
   ሀ. የረዳት ኮሚሽነሮችን ምደባ በሥራ አስፈፃሚ እንዲጸድቅለት ለፕሬዝዳንቱ ያቀርባል፣
   ለ. የኮሚሽኑን መተዳደሪያ ደንቦች ያስፈጽማል፣
   ሐ. በክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን አቤቱታ ሰሚ አካል እና በዲስፕሊን ኮሚቴ የሚሰጡ ውሳኔዎችን እንዲሁም በየደረጃው የሚቀረቡለትን አቤቱታ አይቶ ይወስናል፣
   መ. የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ እቅድና ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ጉባኤ ያቀርባል፣
   ሠ. ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ የኦዲትና የኢንስፔክሽን ሥራዎች እንዲሠሩ ያደርጋል፣
   ረ. የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አሠራርና አቅም ግንባታ የሚመለከቱ ጥናቶች፣ የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶች እንዲሁም የማረሚያ ጥበቃ ሙያና አገልግሎት ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

www.chilot.me

ሰ. በክልሉ ማረሚያ ኮሚሽንና በፌዴራል ማረሚያ ኮሚሽን እንዲሁም ከሌሎች ክልል ማረሚያ ቤቶች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፤

ሸ. የኮሚሽኑን የአመራር ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል፤

ቀ. ኮሚሽኑን አስመልክቶ የውጭ ግንኙነት ያደርጋል።

## ክፍል ሦስት
## ስለ ሐረሪ ሕዝብ ክልል ማረሚያ ጥበቃ አስተዳደር

### 10 ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. በክልሉ ማረሚያ ጥበቃ አባልነት ለመመልመል ፈቃደኛ የሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚከተሉትን መመዘኛዎች በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል።

   ሀ. ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና ለክልሉ ህገ- መንግስት ተገዥ የሆነ፤

   ለ. ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት ለመመልመል የሚያበቃ የትምህርት ደረጃ፣ አካላዊ ብቃትና የተሟላ ጤንነት ያለው፤

   ሐ. መልካም ሥነ- ምግባር ያለው፤

   መ. በፍርድ ቤት የተወሰነ የወንጀል ጥፋተኝነት የፍርድ ሪኮርድ የሌለው፤

   ሠ. እድሜው ከ18 ዓመት ያላነሰ ሆኖ ጣሪያው በመመሪያ ይወሰናል፤

   ረ. የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ስልጠናን ያጠናቀቀ፤

   ሸ. የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚችል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመለመለ ማንኛውም ዜጋ የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆነ እንደሆነ በማረሚያ ጥበቃ ሲቀጠር የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን መተዉ ይኖርበታል።

### 11.ቃለ መሃላ ስለመፈጸም

ለማረሚያ ጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ማንኛውም ምልምል ለፌዴራሉና ለክልሉ ሕገ- መንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ሙያዊ ሃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሐላ ይፈጽማል፤ የቃለ መሐላው ይዘት በደንብ ይወሰናል።

### 12 የአገልግሎት ዘመን

1. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት አመት ይሆናል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

2. የማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ ቅጥር ከሚከተሉት መካከል በማናቸውም ምክንያት ይቋረጣል።

   ሀ. በሞት፤

   ለ. በደንቡ መሰረት የስንብት ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ፤

   ሐ. በሐኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ሕመም ወይም የአካል ጉዳት ለሥራው ብቁ ሳይሆን ሲቀር፤

   መ. በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በደንቡ መሰረት ወንጀሉ ለስራው ብቁ እያደርገውም ተብሎ ሲወሰን፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

   ሠ. በሥራ አፈጻጸም ወይም በዲስፕሊን ጥፋት፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

   ረ. በጡረታ ሲገለል።

### 13 መብት

1. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል

   ሀ. በመንግስት በሚጸድቅ የደመወዝ እስኬል መሠረት ደመወዝ ያገኛል፤

   ለ. በኮሚሽኑ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቀለብ፣ ልዩ ልዩ አበሎች፣ የደንብ ልብስና የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

   ሐ. በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፤

   መ. ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በመ/ቤቱ ወጭ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

   ሠ. ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሙሉ ወይም ከፊል የመስራት ችሎታውን በዘላቂነት ያጣ የማረሚያ ጥበቃ አባል አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል።

2. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል

   ሀ. መብቱን በተመለከተ የበላይ ሃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፣ ስህተት ሲያይ የመጠቆም እና ችግሮችን በውይይት የመፍታት መብት አለው፤

   ለ. የሥልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

### 14. ግዴታ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል

1. በፌዴራሉና በክልሉ ሕገ - መንግስት ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች መሠረት የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብቶችና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ በማክበር እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ሥራውን የማከናወን፤

2. ሥራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ የማሳየት ግዴታ አለበት።

### 15. የጡረታ መውጫ እድሜ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በጡረታ የሚገለልበት እድሜ ጣሪያ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት ለመንግስት ሠራተኞች የተወሰነው የጡረታ መውጫ እድሜ ይሆናል።

### 16. ስለ ክልሉ ማረሚያ ቤቶች አቤቱታ ሰሚ

በኮሚሽኑ ውስጥ አቤቱታ የሚሰማ የሐረሪ ክልል ማረሚያ ኮሚሽን አቤቱታ ሰሚ አካል ይቋቋማል፤ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

www.chilot.me

## 17. ስለ መተዳደሪያ ደንብ

የክልሉ የማረሚያ ጥበቃ አባሎች መተዳደሪያ ደንብ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ይወጣል::

## ክፍል ሶስት
## ስለ ታራሚዎች አያያዝ

## 18. መርህ

1. ታራሚዎች ሠብዓዊ ክብራቸው በተጠበቀ ሁኔታ የመያዝ መብት አላቸው፤
2. የታራሚዎች አያያዝ ታራሚዎች የተወሰነባቸውን ቅጣት ጨርሰው ሲወጡ ሕግ አክባሪ ሆነው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችላቸው መሆን ይኖርበታል፤
3. በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ያሉ እንዲሁም የፍትሐ ብሔር ታራሚዎች ከወንጀል ድርጊት ነፃ እንደሆኑ ተቆጥረው በወንጀል ቅጣት ከተወሰነባቸው ታራሚዎች ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል::

## 19. ታራሚን ስለመቀበል

በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ኮሚሽኑ ማንኛውንም ሰው በማረሚያ ቤት እንዲቆይ መቀበል የለበትም።

## 20. ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ስለመሆኑ

በታራሚዎች መካከል በፆታ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ አመለካከት ፣ በብሔር ብሔረሰብ አባልነት ወይም በማህበራዊ ምንጭ ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

## 21. ታራሚዎችን በደረጃ ለይቶ ስለመያዝ

1. ሴት ታራሚዎች ከወንድ ታራሚዎች ሙሉ በሙሉ የተለየ ክፍሎች ይኖራቸዋል ፤
2. ሁኔታው በፈቀደ መጠን ታራሚዎች በእድሜአቸው፣ በፈጸሙት ወንጀልና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል።

## 22. የታራሚዎች ክፍሎች ሁኔታ

1. ታራሚዎች የሚኖሩባቸው ክፍሎችና ግቢያቸው በጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል ንጹህ አየርና በቂ ብርሃን የሚያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/እንደተጠበቀ ሆኖ የታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎች ሲዘጋጁ ታራሚው በሚያሳየው የባህሪ ለውጥና በወንጀል ድርጊት የመፀፀት ሁኔታ እኳያ ለይቶ ለመጠቀም የሚያስችሉና ታራሚዎችን በቀና ተወዳዳሪነት መንፈስ ወደ መታረምና ተሃድሶ የሚያተጉ ሊሆኑ ይገባል።

## 23. ስለምግብና የጤንነት እንክብካቤ

ታራሚዎች በተቻለ መጠን ጤናቸውን ለመጠበቅ የሚያበቃቸውን በቂ ምግብና አስፈላጊ የሕክምና አገልግሎት በነፃ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## 24. ሕፃን ልጅ ስለአላት ሴት ታራሚ

1. ለልጁ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እድሜው ከአሥራ ስምንት ወራት ያልበለጠና የእናቲቱ የቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው ህፃን ከሴት ታራሚ እናቱ ጋር አብሮ ማረሚያ ቤት ሊገባ ይችላል፤
2. ኮሚሽኑ ለልጁ ጤንነትና እንክብካቤ አስፈላጊውን የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
3. የእናቲቱ የእስር ቆይታ በልጁ አካላዊ ወይም ሥነ-ልቦናዊ አቋም ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ሆኖ ሲገኝ ህፃኑ አሳዳጊ ወይም ምግዚት እንዲያገኝ ኮሚሽኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

## 25. ከጉብኝዎች ጋር ስለመገናኘት

ታራሚዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከሕግ አማካሪዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር የመገናኘት መብት አላቸው፤ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## 26. ስለመታሠርና ዝውውር መረጃ የማስተላለፍ መብት

ማንኛውም ታራሚ መታሰሩን ወይም በማናቸውም ምክንያት ከታሰረበት ተቋም ወደ ሌላ ተቋም መዛወሩን ወዲያውኑ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚፈልገው ሰው የመናገር መብት አለው::

## 27. በሥራ ስለማሰማራትና ስለ ፈቃድ

1. በፍርድ ቤት የተወሰነበትን ቅጣት በማረሚያ ቤት በመፈፀም ላይ ያለ ማንኛውም ታራሚ ከችሎታውና ከሙያው ጋር የሚስማማና ጤንነቱን የማይጎዳ ተመጣጣኝ ሥራ እንዲሰራ ይደረጋል፤ በኮሚሽኑ በሚወጣ መመሪያ መሰረት እንደሁኔታው ለሥራው ክፍያ ያገኛል፤
2. ታራሚዎች በማረሚያ ጥበቃ አባል አጃቢነት ለልዩ ልዩ ማህበራዊ ችግሮቻቸው ማቃለያ ፈቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል::

## 28. የታራሚ ግዴታዎች

ለጥበቃ ሥራ ሥነ-ሥርዓት አከባበር፣ ጽዳት፣ ጤና አጠባበቅ፣ ማህበራዊ ግንኙነትና ስለሌሎችም ጉዳዮች በሚወጣ ደንብ የሚገለፁ የሥነ-ሥርዓት ግዴታዎችን ታራሚዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው።

## 29. የወንጀል ድርጊት

ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

www.chilot.me

## ክፍል አምሥት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 30 ኮሚሽኑ ከፌዴራል ማረሚያ ኮሚሽን ጋር ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት

1. የማረሚያ ቤቶችን አስተዳደርና አሠራር የታራሚዎችን አያያዝና አጠባበቅ ለማሻሻል እንዲሁም ለማረሚያ ጥበቃ አባሎችና ሠራተኞች የስልጠና እድሎችን ለማመቻቸት ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ጋር ግንኙነት ያደርጋል ፤
2. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን በሚያዘጋጀው የጋራ ጉባኤ ላይ ይሳተፋል ፤
3. በጋራ ጉባኤው የማረሚያ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመገምገም የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤ የአሠራር ደንብና መመሪያዎች በይዘት ረገድ እንዲሻሻሉና ወጥነት እንዲኖራቸው የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል፤
4. የማረሚያ ጥበቃ የስልጠና አቅጣጫ ይዘትና ደረጃን በሚመለከት በጋራ ይቀይሳል፤
5. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽንና የክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ኃላፊዎች በጋራ ጉባኤው ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች በክልሉ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤
6. ኮሚሽኑ የታራሚዎችን አጠቃላይ ሁኔታ በሚመለከት ሪፖርትና ስታትስቲክ ለክልል ሲልክ በግልባጭ ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ያስተላልፋል።

### 31፣ ወታደራዊ ማዕረግ ስለመቅረቱ

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የማረሚያ ጥበቃ አባል ወታደራዊ ማዕረግ አይኖረውም ሆኖም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሆነ ማዕረግና ምልክት ይኖረዋል ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤
2. ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሥራ መደቡን የሚያመለክት የመለያ ደንብ ልብስ እንዲሁም ማንነቱን የሚገልጽ ስሙን፤ መለያ ቁጥሩን፤ ክፍሉንና ኃላፊነቱን የያዘ ባጅ ወይም ምልክት ይኖረዋል።

### 32. አሠራር

1. የኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር ዋና ተግባር አፈፃፀም አቅጣጫ ይሆናል፤ የ ቡድን አሠራሮች የጋራና የነጠላ ኃላፊነትን ያስከትላሉ፤
2. በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው፤
3. የኮሚሽኑ አሠራር የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህ የተከተለ እንዲሁም የህዝብ ተሳትፎን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

### 33. የተከለከለ ድርጊት

ማንኛውም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ድርጊት የተከለከለ ነው።

### 34. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል።

### 35. የሒሳብ መዛግብትና የሒሳብ ምርመራ

1. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ኦዲት ይደረጋሉ።

### 36 ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ ለዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ በዚህ ለዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### 37. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

### 38 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት 1/ ቀን 1996 ዓ.ም
ፋሰድ ኢብራሂም
የሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መንግሥት ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

**OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE**

፰ኛ ዓመት ቁጥር 9
8th year No 9

ሐረር መጋቢት 1/1996
HARAR 11th March 2004

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ<br>Unit price 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር<br>P.O.Box 272 |


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር 40/1996 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፀጥታ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ-----------ገጽ327


## አዋጅ ቁጥር 40/1996

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፀጥታ ም/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል እስከአሁን ሲያጋጥሙ የነበሩ የፀጥታ ችግሮችን ለመፍታት የክልሉ መንግሥት ከፌደራል ፀጥታ ኃይሎች ጋር ሲያደርገዉ የነበረው እንቅስቃሴ አተጋቢ ቢሆንም ቅንጅታዊ አሠራሩ አስተማማኝ ባለሆነ የታወቀመመሪያና ወጥነት በሌለው መልኩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ብቻ የሚያገለግል መሆኑን በመገንዘብ፡

ሲሠራበት የቆየዉን አካሄድ ችግርችን በተገቢዉ ሁኔታ ለመፍታት በሚያስችል ቋሚና በህግ በተደገፈ የፀጥታ አደረጃጀት በክልልና በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ በማደራጀት የፀጥታን ጉዳይ የሚከታተልና አቅድ የሚያቀናጅ አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፡

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26/2/ፊ/ መሠረት የሚከተለዉ ተዉጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ « የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፀጥታ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 40/1996» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፤

1. «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (1)(9) ላይ የተመለከተው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ነዉ.
2. «ሥራ አስፈጻሚ» ማለት በክልሉ ህገ መንግሥት መሠረት የተቋቋመው የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈጻሚ አካል ነዉ፡፡
3. ምክር ቤት ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመዉ የክልሉ መንግሥት የፀጥታ ምክር ቤት ነዉ

### ክፍል ሁለት

### የፀጥታ ምክር ቤት ስለ ማቋቋም

**3/ መቋቋም**

የፀጥታ ጉዳይ የሚከታተል፣እቅድ የሚያቀናጅ እና የሚመራ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፀጥታ ምክር ቤት በርዕሰ መስተዳደሩ ጽህፈት ቤት ሥር የህግ ሰዉነት ያለዉ የክልሉ መንገስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**4/ ዓላማ**

የፀጥታው ምክር ቤት ዓላማ በክልሉ የሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ የፀጥታ ችግሮችን የክልሉ መንግሥትና የፌደራል የፀጥታ ሃይሎች ተደራጅተው

www.chilot.me

በጋራ ለመፍታት የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር እንዲፈጠር በማድረግ የክልሉ ደህንነትና ፀጥታ መከበሩን ማረጋገጥ ይሆናል::

## ክፍል ሦስት

### የፀጥታዉ ምክር ቤት አደረጃጀት

**5. የፀጥታዉ ምክር ቤት አቋም**

የፀጥታዉ ምክር ቤት:

1. የፀጥታዉ ምክር ቤት አመራርና አባላት
2. በተዋረድ የሚቋቋሙ የፀጥታ ምክር ቤቶች እና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል::

**6/ የፀጥታዉ ም/ቤት አመራርና አባላት**

የፀጥታዉ ምክር ቤት የሚከተሉት ቋንጅታዊ አካላት ይኖሩታል:

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር-------------ሰብሳቢ
2. የክልሉ ፍትህና ፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ-----ም/ሰብሳቢ
3. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር --------------ፀሐፊ
4. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም-------አባል
5. የክልሉ ሚሊሺያ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ--አባል
6. የፌደራል ፖሊስ /በክልሉ የተመደበ/ኃላፊ---አባል
7. የደህንነት የክልሉ ተጠሪ ------------አባል
8. የመከላከያ /በክልሉ ካሉት/ ከፍተኛ የሠራዊት አዛዥ----------------------- አባል

**7/ ተጠሪነት**

1. የፀጥታው ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ይሆናል
2. የክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለርእሰ መስተዳድሩ ይሆናል
3. የክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የፀጥታዉን ምክር ቤት ሥር ይመራሉ ያስተባብራሉ::

**8/ ተግባርና ኃላፊነት**

የክልሉ ፀጥታ ምክር ቤት የሚከተሉትተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

1. በክልሉ ዉስጥ ለፀጥታ ችግር ጠንቅ የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉትን ችግሮች በዝርዝር በመገምገምና በመተንተን መፍትሄ ያስቀምጣል:

   ለተግባራዊነቱ የቅንጅት እቅድ በማዉጣት በገለጸ የሥራ ክፍፍል ይንቀሳቀሳል:
2. የክልሉን የፀጥታ ሁኔታ በሚመለከት የመረጃ ልዉዉጥ ያደርጋል: ከሁሉም አካላት የሚገኘ ዉን መረጃ ለፀጥታዉ አጠባበቅ መነሻ በማድረግ የፀጥታ ጥበቃ እቅድ በማዉጣት ተግባራዊ ያደርጋል:
3. በክልሉ ዉስጥ ያሉ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸዉ ተቋማት በቂና የተስተካከለ ጥበቃ ያላቸዉ መሆኑን ያረጋግጣል:
4. የህዝቡን የፀጥታ ሥነ አእምሮ ለማዳበር የሚያስፈልጉ ሥራዎችንና በየሆቴሉና በግል ተቋማት የተቀጠሩ የጥበቃ ሠራተኞችን የማሰልጠን ከፖሊስ ጋር የታወቀ ግንኙነት የመፍጠርና የሪፖርት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን መከታተል፤በክልል ደረጃ አንድ ወጥ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል:
5. በክልሉ የሚያልፉ ዋና ዋና መንገዶችን በምንም መልኩ በታጠቀ ይሁን ባልታጠቀ ዘራፊ እንቅስቃሴን የማወክ ተግባራት እንዳይፈፀም የፀጥታ ሃይሉን ከገጠሩ የሚሊሺያ ሃይል ጋር አጣምሮ አርገጠኛ ጥበቃ ያላቸዉ መሆኑን ያረጋግጣል:
6. ህገወጥ የትጥቅ዗ዝዉዉርና ንግድን ይከታተላል በተገኘበትም ለህግ እንዲቀርብ ያደርጋል:
7. በክልሉ ዉስጥም ሆነ ከክልል ክልል ሊያገጥሙ የሚችሉ የገላ ግጭቶችን አስቀድሞ በማወቅ ወደ ግጭት ከማምራቱ አስቀድሞ መፍትሄ መስጠት: ከክልል ክልል ቢሆንም ተገናኝቶ ይሠራል:
8. ፀጥታን በሚመለከት ከክልሉ የፀጥታ ምክር ቤት አቅም በላይ የሚሆን ወይም ተጨማሪ ቅንጅት የሚጠይቅ ሁኔታ ተፈጥሮ ሲገኝ በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አማካኝነት ከፌደራል የፀጥታ ምክር ቤት ጋር አስፈላጊዉን ቅንጅት ያደርጋል: ለዚህ እንዲመችም በየጊዜዉ ስለ ክልሉ የፀጥታ ሁኔታ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ያሳዉቃል::
9. ፀጥታን በሚመለከት በቅንጅት የወጣዉን እቅድ በሥራ ክፍፍሉ መሠረት ተግባራዊ መደረጉን ይገመግማል፤ ዉሳኔ ያስተላልፋል::
10. በተዋረድ ለሚቋቋሙት የፀጥታ ምክር ቤቶች ሥራ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል፤ በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል:
11. በተዋረድ በሚቋቋሙ የጸጥታ ምክር ቤቶች የተከናወኑ የሥራ ሪፖርቶችን ያዳምጣል::

**9/ በተዋረድ ስለሚቋቋሙ የፀጥታ ምክር ቤቶች**

በተዋረድ የሚቋቋሙ የፀጥታ ምክር ቤቶችን አመራር፤አደረጃጀትና አሠራር የሚመለከቱ ጉዳዮች በደንብ ይወሰናል::

## ክፍል አራት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**10.ደንብ የማዉጣት ሥልጣን**

የሥራ አስፈጻሚ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊዉን ደንብ ለማዉጣት ይችላል::

**11.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1996

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፕሬዝዳንት

www.chilot.me